AMN
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3529 | ቅዳሜ ሐምሌ 12 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# “በሀሳብ ልውውጥ የሚመጣው ሰላም መሰረቱ ጠንካራ ነው”

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

7


ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

## የአረንጓዴ ሽፋኑ መጨመር አንድምታ



8
ፎቶ-ከፋይል
መዲናዋ የምትተክለው የችግኝ መጠን ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል

## ምግባቸውን እያመረቱ ያሉ ከተሞች


4
ፎቶ- ከገፀ ድር
ከሲንጋፖር ከተማ የከተማ ግብርና ስራዎች አንዱ

## ክረምትና ኪነ ጥበብ


13
ፎቶ- ከገፀ ድር
የክረምትና ኪነ ጥበብን ትስስር ከሚያሳዩ የሀገራችን የጥበብ ስራዎች መካከል አንዱ

# ትውልድ የሚታነፅባቸው ፕሮጀክቶች

- በዓመቱ ከ5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ 150 የትምህርት ፕሮጀክቶች መከናወናቸው ተጠቆመ


ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የትምህርት ፕሮጀክቶችን በመረቁበት ወቅት

በሸዋርካብሽ ቦጋለ

በቀደሙት ዓመታት ደካማ እና ስሁት በሆነ ፖሊሲ ክፉኛ ከተጎዱ ዘርፎች መካከል ትምህርት አንዱ ነው። በተለይ ከለውጡ በፊት የነበረው ስርዓት ቀርጾ ሲተገብረው የቆየው ፖሊሲ በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ስለማድረሱ ተደጋግሞ ይነገራል። ነገር ግን ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ በተወሰዱ ተከታታይ የማስተካከያ እርምጃዎች ዘርፉ ላይ መሻሻል መጥቷል።

በ2017 በጀት ዓመት ብቻ ከ5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ 150 የትምህርት ፕሮጀክቶች ተከናውነዋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ሐምሌ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ተመርቀዋል፤ በ2018 ትምህርት ዘመን ወደ ተሟላ አገልግሎት እንደሚገቡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ያሰፈሩት መልዕክት ያመላክታል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# እፎይታን የቸረው ህይወት አድን ስራ

- ሆስፒታሉ ከኩላሊት እጥበት ህክምና ባሻገር በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ንቅለ ተከላውን ለመጀመር አቅዷል

በስንታየሁ ምትኩ

ወጣት ስዩም ቃለአብ በ2006 ዓ.ም አንድ ቀን ስራ ውሎ ወደ ቤት እየተመለሰ እያለ ነበር ከአፍንጫው ደም መፍሰስ የጀመረው፡፡ “ቤት ደርሼ እረፍት ሳደርግ ህመሙ ይሻለኛል” ብሎ ቢያስብም ከአቅም በላይ ሆነበት። ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ምርመራ ሲደረግለትም ኩላሊቶቹ ሙሉ ለሙሉ ስራ ማቆማቸውን አወቀ፡፡

ወደ ገጽ 11 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ




## ለትምህርት ጥራት መሻሻል ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ሲተገበር የቆየው የትምህርት ፖሊሲ ትውልዱ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት አድርሷል። በተለይ በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ላይ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ ነገር ግን ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ በተወሰዱ ተከታታይ የማስተካከያ እርምጃዎች ዘርፉ ላይ መሻሻል መጥቷል። የትምህርት ፍኖተ ካርታ ማሻሻያው፣ የ'ትምህርት ለትውልድ' ንቅናቄ፣ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እና የምገባ መርሃ ግብር የትምህርት ጥራትን እና ተደራሽነትን እያሻሻሉ ነው፡፡

በ2017 በጀት ዓመት ብቻ ከ5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ግንባታቸው ተጠናቅቆ ሐምሌ 11 ቀን 2017 ዓ.ም የተመረቁት 150 የትምህርት ፕሮጀክቶች የተግባር አስረጅዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች፤ በ2018 ትምህርት ዘመን ወደ ተሟላ አገልግሎት ይገባሉ፡፡ ፕሮጀክቶቹ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ 14 አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ይዘዋል፡፡ በ64 ነባር ትምህርት ቤቶች ላይ የተከናወኑ 1 ሺህ 655 የመማሪያ ክፍሎችን አካትተዋል፡፡ በተጨማሪም የአይ.ሲ.ቲ ክፍሎች፣ ቤተ ሙከራዎች፣ የመመገቢያ አዳራሾች፣ ቤተ መፅሐፍት፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ ምድረ ግቢዎችን ፅዱና ውብ፣ የመጸዳጃ ቤቶችን እና የውሃ አገልግሎትን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና መምህራን ምቹ የሚያደርጉ ስራዎችን ያካተቱ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ያሰፈሩት መልዕክት ያመላክታል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ እንደ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)፣ የጫማ፣ የደብተር እና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሶችን ለተማሪዎች በማመቻቸቱ የትምህርት ጥራት ላይ የነበሩ ክፍተቶች እንዲደፈኑ እየተደረገ ነው፡፡ በቀዳማይ ልጅነት ላይ የሚደረገው ርብርብም ሌላ አቅም የሚፈጥር ዕድል ነው፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ በትኩረት እየተሰራ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል 10 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል። የቅድመ 1ኛ ደረጃ ተማሪዎች የማስተማር ስነ ዘዴ ጨዋታን መሰረት ያደረገ መሆኑ ተማሪዎች ለቀጣዩ እርከን ዝግጁ እንዲሆኑ በማስቻል ለትምህርት ጥራት መሻሻል እያገዘ ነው፡፡

የተማሪዎች ምገባም የትምህርት ሽፋንና ተሳትፎን እንዲሁም በትምህርት ገበታ ማቆየት (መጠነ መድገምና መጠነ ማቋረጥ) እና የትምህርት ጥራት መሻሻል ላይ ከፍተኛ የሆነ ሚና ተጫውቷል፡፡ በ2017 የትምህርት ዓመት ከ840 ሺህ 585 በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ ምገባ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዚህም ተማሪዎች እኩልነት ተሰምቷቸዋል፤ አንድ አይነት ምሳ ይበላሉ፡፡ ቁርስ በመጠበቅ ምክንያት የሚያረፍዱ ተማሪዎች ቁጥር ትርጉም ባለው ደረጃ ቀንሷል፡፡

እነዚህ ጥረቶች በ2017 የትምህርት ዓመት ቀላል የማይባል ውጤት ማስገኘታቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡ በትምህርት ዘመኑ በየትምህርት ቤቱ የተካሄደው ድጋፍና ክትትል የተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር እንዲሻሻል አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ አስተዳደሩ ባሳለፍነው የትምህርት ዓመት በ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ላስመዘገበው አበረታች ውጤትም ሆነ በከተማ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በበይነ መረብ ተሰጥቶ በስኬት የተጠናቀቀው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና በዘርፉ ላይ የተሰራው ተከታታይ ማሻሻያ ያስገኘው ውጤት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በከተማዋ ካሉ ተማሪዎች መካከል ከ65 እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ይማራሉ፡፡ ለዚህ በትምህርት ቤቶቹ ያሉትን ጫናዎች መቀነስ ላይ እየተሰራ ነው፡፡ አዳዲሶቹ ትምህርት ቤቶች በዚህ ረገድ ከፍተኛ አጋዥ ይሆናሉ፡፡ ይህ ጥረት የተሟላ ውጤት ያስገኝ ዘንድ ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## አብሮ ቢታሰብበት!

### መስከረም ከጉለሌ

በተለምዶ ጊዮርጊስ በሚባለው አካባቢ በሚገኘው የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ፊት ለፊት ወደ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ አራት ኪሎ እንዲሁም መገናኛ ለመሄድ የተዘጋጀን ተሳፋሪዎች ቆመን ታክሲ እየጠበቅን ነበር፡፡ ከምንጠብቀው መካከል የስራ ሰዓት በተለያየ ምክንያት ያለፈባቸው፣ የተለያየ ጉዳይ ያለባቸው በአንድም በሌላ ይቁነጠነጣሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በቦታው የነበሩ እድሜያቸው ገፋ ያለ ለእግር ጉዟቸው ምርኩዝ የያዙ አንድ አባት ቁልቁል መንገዱን እየተመለከቱ ወደ አራት ኪሎ ተጓዙ። በቦታው የነበረ መንገደኛ የመንገዱን ስፋት እና ምቹነቱን እያነሳ የታክሲ መሳፈሪያ አለመኖሩ ተገቢ እንዳልሆነ ይናገራል፡፡

ከአስኮ መስመር የመጣችው አንዲት ተሳፋሪ መዳረሻዋ በተለምዶ እንግሊዝ ኤምባሲ አካባቢ ሲሆን ከተሳፈረችበት ታክሲ የመጨረሻ የወረደችው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት እና ኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ቤት ወይም በቀድሞ አጠራሩ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በር ላይ ነው። የምትሄድበት ቦታ በአስቸኳይ መድረስ ስላለባት የመገናኛን ታክሲ ለማግኘት መነሻቸው ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል ቢሆንም ርቀቱን በመሸሽ ነበር ቦታው ጋ የተገኘችው።

በርግጥ የታክሲም ሆነ የሕዝብ የከተማ አውቶብስ መሳፈሪያ ተርሚናሎች ከኮሪደር ልማቱ ጋር በመተሳሰር መሰራታቸው የምንሄድበት ቦታ ትራንስፖርት ለመያዝ ያለምንም ግርታ መሳፈር አስችሏል። እንኳንስ በቀን በምሽትም ያለምንም ስጋት በእግር መጓዝ የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ነገር ግን ታክሲ የሚጠቀሙ ተሳፋሪዎች ከአንዱ አካባቢ ወርደው ሌላኛውን ለመያዝ በአንዳንድ ስፍራዎች ሲቸገሩ ይታያሉ፡፡ በተለይ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ልጅ የያዙ እናቶች ሲሆኑ ራቅ ያለ ሌላ ቦታ ሄዶ ለመያዝ ይቸገራሉ፡፡

አንዲት ወዳጄም የነገረችኝ ይህንን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ከጉለሌ ሸገር መናፈሻ አካባቢ ተነስታ በተለምዶ ገርጂ መብራት ሀይል ወደሚባለው አካባቢ ለመሄድ ከአዲሱ ገበያ ታክሲ ይዛ ፒያሳ የታክሲ የመጨረሻ ማውረጃው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው፡፡ ቀጥላ የመገናኛ ታክሲን ፒያሳ ጣይቱ ሆቴል (የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሎተሪ አገልግሎት) ፊት ለፊት በመያዝ የካ ክፍለ ከተማ በተቃራኒው ባለው መንገድ ወረድ ብሎ ያወርዳታል፡፡ ከዚህ በኋላ በተለይ የገርጂ ታክሲን ለመያዝ ከቦሌ ክፍለ ከተማ ጀርባ አልፎ ሄዶ መሳፈር እንደሚጠይቅና የእግር መንገዱ ረዘም ያለ እንደሆነ በደከመ መንፈስ አወጋችኝ።

እኔም ጉዞ ሳደርግ የታዘብኩት ገጠመኝ ካሉት የተለየ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገር ይህንን አጋጣሚ የግል የትራንስፖርት ሰጪዎች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሞክሩ ይታያል።

ከተማችን አዲስ አበባ እያሳየችው ያለው ለውጥ እንኳንስ ለነዋሪው ለሌሎችም፣ የሚያስደንቅ ነው፡፡ በኮሪደር ልማቱ የተሰሩ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታዎች ለህብረተሰቡ፣ ለአሽከርካሪው እና ለአገልግሎት ሰጪው ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ በተለይም የኮሪደር ልማት ዋና ዓላማው ከተማችንን ለመኖር ምቹ ማድረግ፣ ገጽታዋን ማሻሻል እና ከልማቱ ማንም ወደ ኋላ ሳይቀር ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ከዚህ ድንቅ ስራ ጎን ለጎን የታክሲ መጫኛና ማውረጃ የሚገኙባቸው ስፍራዎች (በተለይም ከአንድ ታክሲ በላይ ለሚጠቀሙ) ቀረብ የሚልበት እድል ቢኖረው መልካም ነው እላለሁ፡፡


አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ
ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሰገነት አስማማው

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ትውልድ... ከገፅ 1 የዞረ

ፕሮጀክቶቹ ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩ 14 አዳዲስ ትምህርት ትቤቶች፣ 64 ነባር ትምህርት ቤቶች ላይ በማስፋፊያ ስራ የተገነቡ 1 ሺህ 655 የመማሪያ ክፍሎች፣ የአይ.ሲ.ቲ ክፍሎች፣ ቤተ ሙከራዎች፣ የመመገቢያ አዳራሾች፣ ቤተ መፅሐፍቶች፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ ምድረ ጊቢዎችን ፅዱና ውብ የማድረግ ስራ፣ የመጸዳጃ ቤቶች እና የውሃ አገልግሎትን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና መምህራን ምቹ የማድረግ ስራዎችን ያካተቱ ስለመሆናቸው ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በመልዕክታቸው ጠቁመዋል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች የ2017 የትምህርት ዘመን እቅድ አፈጻጸም ግምገማዊ ስልጠና እና የ2018 ዓ.ም እቅድ ውይይት አካሂዶ ነበር፡፡ በዚህ መድረክ የስራ አቅጣጫ የሰጡት የቢሮው ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር)፣ በ2017 የትምህርት ዘመን በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ጠቁመው፣ በዚህም ቀላል የማይባል ስኬት መመዝገቡን ተናግረዋል፡፡

በ2017 ዓ.ም በየትምህርት ቤቱ የተካሄደው ድጋፍና ክትትል የተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር እንዲሻሻል አስተዋጽኦ ማበርከቱን የጠቆሙት ዘላለም (ዶ/ር)፣ በከተማ አስተዳደሩ በዘንድሮው ዓመት በ6ኛ እና 8ኛ ክፍል የተመዘገበው አበረታች ውጤትም ሆነ በከተማ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በበይነ መረብ ተሰጥቶ በስኬት የተጠናቀቀው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በዘርፉ ላይ ሲሰራ የነበረው ተከታታይ ማሻሻያ ያስገኘው ውጤት እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ በትኩረት እየተሰራ ነው ያሉት ዘላለም (ዶ/ር)፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት 10 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል ላይ ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም ለመጣው ውጤት አንዱ ምክንያት ይሆናል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የተከናወኑባቸው ክፍለ ከተሞች በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ረገድ ከቀደሙት ዓመታት ግልፅ ልዩነት እንደሚያመጡም ተመላክቷል፡፡ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ለሊስቱ ተስፋዬ፣ በክፍለ ከተማው በ18 ተቋማት የተገነቡ 50 የትምህርት ፕሮጀክቶች መመረቃቸውን ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቶቹ ለትምህርቱ ዘርፍ መሻሻል የጎላ ጥቅም እንዳለው ተናግረዋል፡፡



ፎቶ ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ ከተማ ተገንብተው ወደ አገልግሎት ከገቡ 150 የትምህርት ፕሮጀክቶች መካከል ከፊሎቹ

ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ መሃል ከተማ የነበሩ በርካታ ነዋሪዎች ወደ ክፍለ ከተማው መምጣታቸውን ተከትሎ በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥርም መጨመሩን ጠቅሰው፣ የተማሪዎች የክፍል ጥምርታ፣ የመፀዳጃ ቤት እንዲሁም ለመማር ማስተማሩ ምቹ የሆነ መሰረተ ልማት ከመፍጠር አኳያ የፕሮጀክቶቹ መመረቅ በርካታ ችግሮችን ይፈታሉ ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት በአንድ ክፍል ከ70 እስከ 130 የሚደርሱ ተማሪዎች ይማሩ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊዋ፣ ችግሩን ለማቃለል በቆርቆሮ በተሰሩ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ እስከመማር ተደርሶ እንደነበር ተናግረዋል፡፡

አሁን የተከናወኑት የማስፋፊያና አዳዲስ ግንባታዎች የተማሪና የክፍል ጥምርታ ከማስተካከል ባለፈ ተማሪዎች ሰፊና በተመቻቸ ሁኔታ የሚማሩበትን ዕድል የሚፈጥር ብሎም የተማሪዎች የክፍል ጥምርታንም ወደ 50 እንደሚያደርሰው አስታውቀዋል፡፡

በተለይ በገላን ጉራ የልማት ተነሺዎች መንደር የተገነባው አብዲ ጃርሶ ትምህርት ቤት ለልማት ተነሺዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት በተሳካና በተመቻቸ መንገድ ለማከናወን የሚያስችል ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ይሰጥበታል፡፡

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በመንግስት የተቋቋሙ 10 ሁለተኛ ደረጃ፣ 17 አንደኛ ደረጃና 17 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ፣ የእነኝህም የቅበላ አቅም ከ1 ሺህ 500 እስከ 1 ሺህ 800 የሚደርስ ነበር፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተጠናቀቁት እነዚህ ግንባታዎች በርካታ መሰረተ ልማቶች የተሟሉላቸው የተማሪዎችንም ሆነ የማህበረሰቡን ችግሮች የፈቱ በትምህርት ጥራት ረገድም ከፍተኛ ፋይዳ የሚያመጡ ናቸው፡፡

የ2017 የትምህርት ዘመን በክፍለ ከተማው ያሉ የግል ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በቀንና በማታው ክፍለ ጊዜ ወደ 200 የሚጠጉ ተማሪዎች እንደነበሩ ያስታወሱት ኃላፊዋ ከፕሮጀክቶቹ ምረቃ በኋላ ግን የተማሪ ቅበላ በእጅጉን እንደሚጨምር ነው የጠቆሙት፡፡

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ በላይ ነጋሽ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው በትምህርት ዘርፍ ብቻ ወደ 16 ግንባታዎች መከናወናቸውን ጠቅሰው፣ እነኝህም ከዚህ በፊት የነበረውን የተማሪ ክፍል ጥምርታ 1 ለ 45 በማመጣጠን፣የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን የሚያረጋግጡ ናቸው ብለዋል።

ትናንት ከተመረቁት በርካታ ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው በክፍለ ከተማው ወረዳ 14 ሃና ፉሪ የተገነባው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ርቀው ሳይሄዱ በአቅራቢያቸው የትምህርት እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስቻለ ነው ያሉት ኃላፊው ወደ 15 ሺህ ካሬ ሜትር በሚጠጋ መሬት ላይ በተከናወነው በዚህ ፕሮጀክት በርካታ የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሁለት ባለ አራት ፎቅ፣ የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች መማሪያ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ ስፖርት ሜዳና የአስተዳደር ህንፃዎችን ማካተቱን ጠቅሰዋል፡፡

ዘላለም (ዶ/ር) በማብራሪያቸው "ከጊዜ ወደ ጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እያመጣን ያለነው እመርታዊ ለውጥ ይበል የሚያሰኝ ነው" ብለው፣ በትምህርት አመራር፣ በመምህራን፣ በትምህርት ባለሙያው፣ በአሰራሩ፣ በአደረጃጀትና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያሉ ህፀፆችና ግድፈቶችን በተደራጀ ስልት መቅረፍ ይገባል፤ ባለፉት ዓመታት ይህን ስናደርግ ነበር ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ትምህርት ክፍል መምህር ውቤ ካሳዬ (ዶ/ር) ይህንኑ ሀሳብ ያጠናክራሉ፣ በትምህርት ዘርፉ ላይ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ነባር ችግሮችን በማቃለል የትምህርት ጥራትና ተደራሽነትን የማረጋገጥ ዕድል እንደሚሰጡ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ ተናግረዋል፡፡

መምህሩ በሰጡን አስተያየት፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በትምህርት ዘርፍ ላይ የተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የሚሄድ ውጤት ያስገኛሉ፡። በተራዘመ ጊዜ ደግሞ ከችግሩ በመውጣት ጠንካራና ተወዳዳሪ ትውልድን የማፍራት አቅም ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ዓመት መጨረሻ ላይ የታየው ውጤትም ችግሮቹ እየተቃለሉ እንደሚሄዱ አመላካች ናቸው ብለዋል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ እንደ ዩኒፎርም፣ ጫማ፣ ደብተር እና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትን ለተማሪዎች በማመቻቸቱ የትምህርት ጥራት ላይ የነበሩ ክፍተቶች እየተሞሉ መምጣታቸውን የጠቆሙት ዘላለም (ዶ/ር)፣ በተለይም የምገባ መርሃ ግብሩ የተማሪዎችን ውጤታማነት አሳድጓል፡፡ የትምህርት አቀባበል አቅማቸው ላይም ልዩነት አምጥቷል የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

"በቀዳማይ ልጅነት ላይ የሚደረገው ርብርብም ሌላ አቅም የሚፈጥር ዕድል ነው። በተጨማሪም የቅድመ 1ኛ ደረጃ ተማሪዎች የማስተማር ስነ ዘዴ ጨዋታን መሰረት ያደረገ መሆኑ ተማሪዎች ለቀጣዩ እርከን ዝግጁ እንዲሆኑ በማስቻል ለትምህርት ጥራት መሻሻል አግዟል" ብለዋል፡፡

እንደ ዘላለም (ዶ/ር) ማብራሪያ፣ በእንግሊዘኛና ሒሳብ ትምህርቶች ላይ የነበረውን ክፍተት ለመድፈን እስትራቴጂ ተነድፎ በጥብቅ ዲሲፕሊን መተግበሩ ለውጤቱ መሻሻል ያበቃ ሌላው ምክንያት ነው፡፡ በ2017 የትምህርት ዘመን የመጣው መሻሻልም የዚሁ ጥረት ውጤት ነው፡፡

**ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት የሆኑት የትምህርት ፕሮጀክቶች ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩ 14 አዳዲስ ትምህርት ቤቶች እና 64 ነባር ትምህርት ቤቶች ላይ በማስፋፊያ ስራ የተገነቡ 1 ሺህ 655 የመማሪያ ክፍሎችን ያካተቱ ናቸው**

በከተማዋ ካሉ ተማሪዎች መካከል ከ65 እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ይማራሉ። በትምህርት ቤቶቹ ያሉት ጫናዎች ማቅለል ላይ እየተሰራ ነው፡፡ ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት በሚችልበት ልክ እየተሰራበት ነው፡፡

# ምግባቸውን እያመረቱ ያሉ ከተሞች

• ለንደን ከመደበኛው ግብርና አንፃር 70 በመቶ የውሃ ፍጆታ የሚቆጥብ የምድር ውስጥ የከተማ ግብርና ታከናውናለች

**በተካልኝ አማረ**

ከተሞች የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሞተር ናቸው፡፡ በርሚንግሃም ዩኒቨርሲቲ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2023 ያወጣው ጥናታዊ ፅሑፍም ይህንኑ ያመላክታል። ተቋሙ ከተሞች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በከባቢያዊ ስርዓቶቻችን ውስጥ ምን ድርሻ አላቸው? (What are Cities and What Role do They Play in our Social, Economic, and Environmental Systems?) በሚል ርዕስ ያስነበበው ጥናታዊ ፅሑፍ እንደሚያትተው ከሆነ ከተሞች የንግድ፣ የሥራ ዕድል እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ማዕከል በመሆን ለሀገራት ሁለንተናዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ያበረክታሉ፡፡

በዓለም ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (ጂ.ዲ.ፒ) ላይም ከተሞች ትልቁን ድርሻ እንደሚያበረክቱ ይኸው ጥናታዊ ፅሑፍ ያመላክታል። በጥናታዊ ፅሑፉ መሠረት ከተሞች በዓለም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የ85 በመቶ ድርሻ ያበረክታሉ። የተሻለ የመሠረተ ልማት ዝርጋታቸው፣ ግዙፍ ሞሎች፣ መዝናኛ ስፍራዎች፣ የቱሪዝም መስህቦች፣ እንደ ሆቴል፣ ሆስፒታል እና የኮንፈረንስ ማዕከላት ያሉ አገልግሎት አቅራቢዎች ተቋማት ከተሞች ለዓለም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ የሚያስችሏቸው ሀብቶች ናቸው፡፡

በአብዛኛው ተዝናኖታዊ ቅኝት ያላቸው የስራ እንቅስቃሴዎች እንደሚዘወተርባቸው የሚገመተው ከተሞች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግብርናንም እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ መጠቀም ጀምረዋል። አይግሮው ኒውስ፣ 'ምግባቸውን የሚያመርቱ ከተሞች' በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ፅሑፍ፣ የከተማ ግብርና በውስን ቦታ ላይ ትርጉም ባለው ደረጃ የከተማ ነዋሪዎችን አኗኗር እያሻሻለ እንደሚገኝ አስነብቧል፡፡

እንደ ሲንጋፖር፣ ዲትሮይት፣ አትላንታ፣ ሚያሚ፣ ለንደን፣ ኒው ዮርክ እና ፓሪስ ያሉ ከተሞች በአነስተኛ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተለያዩ የግብርና ስራዎችን በመስራት ነዋሪዎቻቸውን ተጠቃሚ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ በዶሮ፣ በወተት፣ በዓሣ፣ በአትክልትና በፍራፍሬ ምርቶች እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ልማት ረገድ ቀላል የማይባል ውጤት አግኝተዋል። ምርቶቹን ለቤት ውስጥ ፍጆታ ከማዋል ባሻገር አቀነባብረው ለሽያጭ በማዋልም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ፈጥረዋል፡፡

የሲንጋፖር ከተማ 10 በመቶ ያህሉን የምግብ ፍጆታዋን በከተማ ግብርና ለመሸፈን በቅታለች፡፡ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2030 ከሚያስፈልጋት የግብርና ምርት ውስጥ 30 በመቶውን በራሷ ለመሸፈን በመስራት ላይም ትገኛለች፡፡ ለዚህም '30 by 30 Goal' የተሰኘ መርሃ ግብር ነድፋ እየሰራች ሲሆን፣ በከተማ ግብርና ዙሪያ ፈጠራን ለማበረታታት 60 ቢሊዮን ዶላር መመደቧን 'World Economice Forum,' "Urban Farms And Food Security In Singapore" በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2021 ያወጣው ፅሑፍ ያትታል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከሲንጋፖር ከተማ የከተማ ግብርና ስራዎች አንዱ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለንደን በምድር ውስጥ የከተማ ግብርና የምታለማው አትክልት



ፎቶ- ከገፀ ድር

የዲትሮይት ከተማ የከተማ ግብርና ስራ አንዱ ማሳያ

ሰማይ ጠቀሶቹ የሲንጋፖር ህንፃዎች በተለያዩ የአትክልት እና ፍራፍሬ ዝርያዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ የግድግዳቸው ዙሪያ እንደ ሐረግ በተንዠረገጉ ልዩ ልዩ የአትክልትና ፍራፍሬ እፅዋት የተሸፈኑ ናቸው፡፡ ጣሪያቸውም 'የግብርና ምርት የሚታፈስባቸው ማሳ' ከሆኑ ሰነባብተዋል።

ሲንጋፖር በክፍት ቦታዎቿ ብቻ ሳይሆን ከመኪና ማቆሚያነት የተረፉ የህፃዎቿን ምድር ቤቶች ሁሉ ሳይቀር ውሃ ሞልታባቸው የዓሳ ማርቢያ አድርጋቸዋለች። በዚህም በመቶ ሺህ ቶን የሚቆጠር የዓሳ ምርት በየዓመቱ ታገኛለች፡፡

ሲንጋፖር በከተማ ግብርና ዘርፍ መሰማራት ለሚሻ ዜጋዋ የገንዘብ ድጋፍ ታደርጋለች፡፡ አትክልትና ፍራፍሬ የማምረት ፍላጎት ላላቸው ዜጎቿ 83 ሚሊዮን ዶላር መመደቧ በመረጃው ተመላክቷል፡፡

የሚቺጋኗ ዲትሮይት በከተማ ግብርና ስራ ቀዳሚ ስፍራን ከሚይዙ ከተሞች ተርታ ትሰለፋለች፡፡ በቀደሙት ጊዜያት የዲትሮይት ከተማ ነዋሪዎች በሰፋፊው ቅጥር ግቢያቸው የውበት እፅዋትን እና ሳር በመትከል ይታወቃሉ፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በእነዚህ ክፍት ቦታዎች ልዩ ልዩ የአትክልት፣ የፍራፍሬ እና የሰብል አይነቶችን በማምረት የምግብ ፍጆታቸውን ወደ ማሟላት ስለመሸጋገራቸው 'One Earth' የተሰኘ ገፀ ድር፣ 'From urban gardens to agrihoods: The rise of agricultural neighborhoods in Detroit' በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2025 ለንባብ ያበቃው ፅሑፍ ያትታል፡፡

በዚህ ፅሑፍ መሠረት፣ 1 ሺህ 400 የዲትሮይት ከተማ ነዋሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የከተማ ግብርና ዘርፍን ተቀላቅለዋል፡፡ እነዚህ የከተማዋ ነዋሪዎች በጓሯቸው በቆሎን ጨምሮ ሌሎች ሰብሎችን፣ ጥራጥሬዎችን፣ አትክልቶችን እና ፍራፍሬዎችን ያመርታሉ፡፡ በዚህም የቤት ውስጥ ፍጆታ ከማሟላት አልፈው ምርቶቻቸውን ለሱፐር ማርኬቶች በማስረከብ ተጨማሪ ገቢ ያገኛሉ፡፡

ለንደን በዘመናዊ የከተማ ግብርና ስራ መልካም ስም እና ዝና እየገነባች ስለመምጣቷ Science Direct ገፀ ድር እ.ኤ.አ በ2023 ያስነበበው ፅሑፍ ያትታል። ለንደን ከሌሎች ከተማዎች በተለየ የምድር ውስጥ የግብርና ቴክኖሎጂን ይዛ ብቅ ብላለች፡፡ ይህም ከግንባታዎች በታች የሚገኘን የምድርን ውስጠኛ ክፍል ለግብርና ስራ ማዋል ነው። ይህ ስራ ከፍተኛ ወጪ፣ ቴክኖሎጂና ጊዜ የሚጠይቅ ቢሆንም ውጤቱ ያማረ ስለመሆኑ በፅሑፉ ተመላክቷል፡፡

ለንደን የምድር ውስጥ ግብርና ያካሄደችው ከመደበኛው የግብርና ስራ በተለየ ጥቅሞችን ስላገኘችበት እንደሆነ የሚያትተው ፅሑፉ፣ በ33 ሜትር ጥልቀት የተዘጋጀው ይህ የከተማ ግብርና ማከናወኛ ዋሻ ከመደበኛው የግብርና ስራ በተለየ የውሃ ፍጆታን 70 በመቶ ይቆጥባል፤ ምርታማነቱ ደግሞ በእጥፍ ይበልጣል (በመደበኛው የምድር ላይ ግብርና በአንድ ሄክታር መሬት 20 ኩንታል ምርት የሚገኝ ሲሆን፣ በምድር ውስጥ ግብርና በሄክታር 40 ኩንታል ምርት ይገኛል እንደማለት ነው)፡፡

> **ከተሞች በዓለም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የ85 በመቶ ድርሻ ያበረክታሉ፡፡ የተሻለ የመሠረተ ልማት ዝርጋታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ከሚያስችሏቸው ሀብቶች ተጠቃሽ ነው**

ይህ ግብርና ያለ አፈር የሚከናወን ሲሆን፣ በአፈር ቦታ ታዳሽ ምንጣፍን ይጠቀማል፡፡ እንደየአትክልት አይነቱ የሚለያይ ቢሆንም በፍጥነት የሚደርሱትን በዓመት አራት ዙር የማምረት ዕድል እንደሚሰጥም ተጠቁሟል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ለከተማ ግብርና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በ3ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔ ላይ የ2017 ዓ.ም አፈፃፀም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፣ የከተማ ግብርናን ከማስፋትና የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን አብራርተዋል፡፡

ማህበረሰቡ በከተማ ግብርና ልማት ስራ ላይ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሆኑን የጠቀሱት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ የተሳታፊዎች ቁጥር እና የከተማ ግብርና ምርትም ስለማደጉ መናገራቸው ይታወሳል። በከተማ ግብርና በዚህ ዓመት ብቻ 280 ሺህ 406 ቶን ምርት ማግኘት ተችሏልም ብለዋል፡፡

እንደ ከንቲባ አዳነች ማብራሪያ 2 ሺህ 188 አርሶ አደሮች በግል ይዞታቸው ላይ በከተማ ግብርና ስራ ተሰማርተዋል። አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ረገድም ጥረት ተደርጓል፡፡ እስከ አሁን በከተማ ግብርና ስራ ውስጥ የታቀፉ የከተማዋ ነዋሪዎች ዶሮ፣ እንቁላል፣ ወተት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ሰብሎችን በማምረት ኑሮአቸውን አሻሽለዋል፡፡

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2050 የዓለም ህዝብ ቁጥር 10 ነጥብ 2 ቢሊዮን እንደሚደርስና የምግብ ፍላጎቱ አሁን ካለው በ70 በመቶ ከፍ እንደሚል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትበያ ያመላክታል። ይህም አማራጭ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ስልቶች እንደሚያስፈልግ ጠቋሚ ነው፡፡ ታድያ የከተማ ግብርና ስራ ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ እሙን ነው።

የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተሜነት መስፋፋት፣ የአካባቢና የአየር ንብረት ተፅዕኖዎች እየተባባሱ መምጣት የምግብ ዋስትና ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ከሚያስገድዱ ምክንያቶች በቀዳሚነት ተጠቅሰዋል፡፡

ችግሩን ለመቋቋም ከተቀመጡ የመፍትሔ አማራጮች መካከል ደግሞ ዘመናዊ የከተማ ግብርናን ማስፋፋት አንዱ ነው። የከተማ ግብርና ምርትና ምርታማነትን በመጠንም በጥራትም በማሳደግ ኢኮኖሚን ይደጉማል፤ በከተማና በከተማ ዙሪያ የሚኖረውን ህብረተሰብ የስርዓተ-ምግብና የምግብ ዋስትና እንዲሻሻልም ጉልህ አበርክቶ እንዳለው ታምኖበት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

# ዘርፈ ብዙ መፍትሔ በ90 ቀናት

**በመለሰ ተሰጋ**

አርክቴክት እና የከተማ ፕላነር ሮበርት ሳሙኤል (ዶ/ር) “Timeless Cities” (ጊዜ የማይሽራቸው ከተሞች” የተሰኘ ድንቅ የምርምር መፅሐፍ አላቸው። በዚህ ስራቸው ከተሞች ሳያረጁ ከዘመን ጋር እየዘመኑ እና የህዝባቸውን አዳጊ ፍላጎት እያሟሉ ከፍ የሚሉበትን ምስጢሮች ተንትነዋል፡፡

ከተሞች አስደማሚ፣ ሰፊና ምቹ ጎዳናዎች፣ ደመቅ ያሉ ሰፈሮች፣ በአረንጓዴ ዕፅዋት የታጀቡ እና ከግፊያውና ውክቢያው ገለል ብሎ ሰው ከራሱ፣ ከወዳጁ እና ከተፈጥሮ ጋር የነፍስ ጨዋታ የሚኮመኩምባቸው የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ትናንትን ከዛሬ አስማምተው የተሰሩ ልዩ ልዩ ግንባታዎች እና ከቴክኖሎጂ የታረቁ አሰራሮች ሊኖራቸው እንደሚገባ ሮበርት (ዶ/ር) በጥናታዊ መፅሐፋቸው ዳስሰውታል፡፡

በመሆኑም ይላሉ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዘላቂ፣ ለኑሮ ምቹ እና የማያረጁ ከተሞችን ለመፍጠር ጊዜ የማይሽረው የከተማ ዲዛይን መርሆዎችን መቀበልና በዚያው ልክ መተግበር ያስፈልጋል፤ ወደ ህብረተሰቡም ቀረብ ብሎ ፍላጎቱን የሚያሟሉ ስራዎችን ማከናወን እንደሚገባም በመፅሐፋቸው አመላክተዋል፡፡

ከተሞች እንደዘመኑ ስልጡን፣ ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ፣ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችሉ፣ የትራፊክ መጨናነቅን የሚቀንሱና ከተፈፅሮ የተዋደዱ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የህዝብ ማመላለሻ አማራጮች የሚጠቀሙ፣ ያልተጨናነቁ የመኖሪያ አካባቢዎች፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ አማራጮችና ፈጠራዎች፣ አካታች ልማትና ማህበራዊ ፍትሕ የነገሰባቸው፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚከተሉ ለነዋሪዎቻቸው ፍላጎትና ምቾት ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆን እንዳለባቸውም ገልፀዋል፡፡

አዲስ አበባም ለህብረተሰቡ ፍላጎት ቅድሚያ የሚሰጡ ዕቅዶችን በማውጣት በርካታ ስራዎችን እያከናወነች ነው፡፡ ጥቂት ዓመታትን ብቻ የኋሊት ብንጓዝ የከተማዋ ማዕከል በሆነው ፒያሳ አሁን የዓድዋ ድል መታሰቢያ የተገነባበት ቦታ ቆሻሻ መጣያ፣ ያልተገቡ ድርጊቶች መከወኛ፣ ራሱ ባክኖ ብዙዎች በሱስና መሰል ነገሮች የሚባክኑበት ስፍራ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ዛሬ ደግሞ የሀገሪቱ የገናናነት ማሳያ፣ የታሪኳ አንጓ የሆነው የዓድዋ ድል ዘወትር የሚዘከርበት፣ በርካቶች እንዳሻቸው የሚዝናኑበት፣ ታሪክን ጨብጠው የሚማሩበት ግሩም ስፍራ ሆኗል፡፡

በአራት ኪሎ ፕላዛ አካባቢ ከልጃቸው ጋር አረፍ ብለው ያገኘናቸው አቶ አማኑ ረታ እንደሚሉት ከተማዋ በከፍተኛ ለውጥ ውስጥ ናት፡፡ ሌላው ቀርቶ በ90 ቀናት የሚሰሩ ልማቶች በሌሎች ዘመናት ዓመታትን ይወስዱ የነበሩ ናቸው፡፡

በዘጠና ቀናት ተግባራትም ሆነ በመደበኛ ዕቅዶች ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ የማድረግ ስራው ለውጡ በግልፅ የሚታይ መሆኑንን መስክረዋል፡፡ በመሆኑም ይላሉ አቶ አማኑ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ ወዳጅነት አደባባይ እና በከተማዋ የተለያዩ ስፈራዎች የተገነቡ የህዝብ መናፈሻና መገልገያዎች ቀደም ሲል ፊታችንን አዙረን እና አፍንጫችንን ይዘን በፍጥነት የምናልፍባቸው ስፍራዎች ነበሩ፡፡ ዛሬ ደግሞ በመልካቸው ተገርመን፣ በመዓዛቸው ተመስጠን፣ ዓይናችንን ብቻ ሳይሆን ልባችንን ከፍተን አረፍ የምንልባቸው ስፍራዎች መሆናቸውን እንመሰክራለን ብለዋል፡፡

በርግጥም በአቀማመጡ ከአዲስ አበባ ዝቅተኛ ቦታ ከሆነው ቦሌ ተነስተን እስከ እንጦጦ ተራራ ከፍ እስከንል ድረስ ትናንት ተጎሳቁለው ይታዩ የነበሩ ስፍራዎች አዲስ ውበትን ተጎናፅፈው እንመለከታለን፡፡ ምቹ እና ሰፋፊ የእግረኛ እና የተሽከርካሪ መንገዶች፣ ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ ውብ መናፈሻዎች፣ የትውልዱን መንፈስ የሚያንፁ የህፃናት መጫወቻ ቦታዎች፣ እንደ አዲስ የመሰራት ያህል የታደሱ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ህንፃዎች፣ በከተማ ግብርና የለሙ ስፍራዎች፣ በአረንጓዴ ዐሻራ ተፈጥሮን የለበሱ አካባቢዎችን እና ከ35 ሺህ በላይ የመዲናዋ ነዋሪዎች በቀን አንዴ የሚመገቡባቸውን የምገባ ማዕከላትን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ስለ ምገባ ማዕከላት ካነሳን አይቀር ወደ ትናንት ተመልሰን ይህንን ታሪክ ማስታወስ ዛሬን በወጉ ለመጨበጥ ያስችለናል፡፡ በአዲስ አበባ መጋቢት 2 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰማው ዜና እጅግ ከባድ ነበር፡፡ በዚሁ ዕለት በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ልዩ ስሙ “ቆሼ” ተብሎ በሚታወቀው ሥፍራ የቆሻሻ ተራራ ተደርምሶ የብዙ ዜጎች ህይወት ጠፋ፡፡

አደጋውን እጅግ አሳዛኝ የሚያደርገው ከቆሻሻ ጋር ተቀላቅሎ የተደፋን ትራፊ ምግብ በልቶ ህይወትን ለማትረፍ እንደ ተራራ በተከመረው ቆሻሻ ዙሪያ ሲጭሩ የነበሩ ችግረኞች ላይ የደረሰ ነበር፡፡ ርሃብ ቀን አይሰጥምና በርካቶች ተርፏቸው የደፉትን ለማንሳት ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ላይመለሱ አሸለቡ፡፡ ይህም ክስተት አዲስ አበባ ከብርቅርቅ እሷነቷ ጀርባ በርካቶች በርሃብ አለንጋ የሚገረፉባት ከተማ መሆኗን የገለጠ ክስተት ነበር፡፡

“ሳይደግስ አይጣላም” እንዲሉ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ዝቅ ብለው የሚያገለግሉ እና ከፍ ያለ ስራን ከውነው የሚያሳዩ አመራሮች እና አሰራሮች ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ የቆሼው አደጋ ከተከሰተ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በአንደኛው ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ወደ ስፍራው አቀኑ፡፡ የሚላስ የሚቀመስ የቸገራቸው ምንዱባኖች ከክምር ቆሻሻዎች ጋር የተቀላቀለ ትርፍራፊ ምግብ ሲመገቡ ተመለከቱ፡፡ የሰው ልጅ በዚህ ልክ ተቸግሮ ማየት ልብን ይነካልና አጋጣሚውን እንደዘበት አይተው አላለፉትም፡፡

በከንቲባዋ አመራር ሰጪነትም የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ከሀሳብ ወደ ተግባራዊ ምዕራፍ ተሸጋገረ፡፡ የበርካቶች መመገቢያ የሆኑትን የምገባ ማዕከላት ለማቋቋም በር ከፈተ። ዛሬ ከ35 ሺህ በላይ የመዲናዋ ነዋሪዎች ቢያንስ በቀን አንዴ በምገባ ማዕከላቱ ሳይሳቀቁ የዕለት ጉርሳቸውን ከ26ቱ የምገባ ማዕከላት ወደ አንዱ ጎራ ብለው ያገኛሉ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የማህበረሰቡን ፍላጎት ታሳቢ በአደረገ መልኩ በከተማ አስተዳደሩ በመደበኛ ዕቅድ ከሚሰሩት በተጨማሪ በዘጠና ቀናትም ሰውን መሰረት ያደረጉ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ባሳለፍነው ማክሰኞም (ሰኔ 24 ቀን 2017 ዓ.ም) ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ90 ቀናት የንቅናቄ ስራዎች ያሉበትን ደረጃ በመገምገም ቀጣይ አቅጣጫዎችን ሰጥተዋል።

ከንቲባዋ ከ15 ቀናት በፊት ከመላው አመራር ጋር በመወያየት ዝርዝር አቅጣጫ የተሰጠባቸው 18ቱም ከተማ አቀፍ የክረምት ንቅናቄ አጀንዳዎች ዙሪያ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ለአብነትም በገበያ ማረጋጋት፣ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በከተማ ግብርናና በሌማት ትሩፋት፣ በገቢ አሰባሰብ፣ የክረምት በጎ ፍቃድ ስራዎች፣ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፣ የሁለተኛ ዙር ኮሪደር ልማት ቀሪ ስራዎችን ቆጥሮ ማጠናቀቅ እና ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆናቸውን በተደረገው ግምገማ ተረጋግጧል።

በተለይም ደግሞ የህብረተሰቡን የኑሮ ጫናዎችን ለማቃለል በተሰራው የተቀናጀ ስራ የከተማዋን የገበያ ማዕከላት፣ የእሁድ ገበያዎች፣ የከተማ ግብርናና የሌማት ትሩፋት ስራዎች፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና መሰል ዘርፎች የምርት አቅርቦት ሰንሰለትን በማሳለጥ ከፍተኛ አበርክቶ እንዲኖራቸው መደረጉም ተገልጿል። ቀሪ ስራዎችን በተሟላ መልኩ ለማሳካት በየደረጃው ያለው አመራር ለላቀ ውጤት በትብብር እንዲረባረብ አቅጣጫም ተሰጥቷል።

በመዲናዋ ሰውን ማዕከል ባደረጉ ልማቶች የከተማዋን ውበት እንደ አዲስ የገለጡ፤ የነዋሪውን ሕይወት ያጣፈጡ በርካታ ስራዎች መከናወናቸውን ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በከተማዋ ከሚኖሩ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት እና ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍል ከተውጣጡ ተወካዩች ጋር በከተማ እና ሀገር አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ በተደረጉ ተከታታይ ውይይቶች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ይህ የልዩ ተልዕኮ አጀንዳ ከሰኔ 5 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም ባሉ 90 ቀናት የሚከናወን ነው፡፡ ንቅናቄው 18 ዋና ዋና ተግባራትን አካትቶ ይዟል። ከእነዚህ የንቅናቄ አጀንዳዎች መካከል የከተማ ግብርናን ማስፋፋት፣ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብርን ማሳካት፣ የክረምት በጎ ፍቃድ ስራዎች፣ የኑሮ ውድነትን መቆጣጠር፣ ሁለተኛ ዙር ኮሪደር ልማትን ማጠናቀቅ፣ የትምህርት ለትውልድ ኢኒሼቲቭ፣ ገቢን ማሳደግ፣ እየተገነቡ የሚገኙ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን (Mega Projects) አጠናቅቆ ለህዝብ ክፍት ማድረግ፣ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ፍትሐዊ አገልግሎትን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ዋና ዋና አቅጣጫዎች እንደሆኑ ተገልጿል።

የከተማ አስተዳደሩን የ90 ቀናት ዕቅድና በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶችን አስመልክቶ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት ማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ማህደር ሳልህ እንደሚሉት ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ እንደ ከተማም ሆነ እንደ ሀገር በዘጠና ቀናት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ቀደም ባሉት ዘመናት ብዙ ዓመታትን ይወስዱ የነበሩ ፕሮጀክቶችን የሚያክሉ ናቸው። በተለይም ሰውን መሰረት ያደረጉ ልማቶች በመሆናቸው ባለፉት ጥቂት ዓመታት የበርካታ ድሃዎችን እንባ ያበሱ፤ ፈገግታቸውንም የመለሱ ስራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ምልከታ በተጎሳቆሉ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በአማረ ሁኔታ ወደተገነቡ ቤቶችና መንደሮች ማዘዋወር፣ ባሉበት ቦታም ቤታቸውን በዘመናዊ መልክ ማደስ፣ የልጆች መጫዎቻ ስፍራዎችን፣ የወጣቶች ስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎች እና መሰል የመናፈሻ ስፍራዎች ተገንብተው ለአገልግሎት ሲበቁ አይተናልም ብለዋል።

ከሰሞኑም የከተማ አስተዳደሩ ለቀጣይ 90 ቀናት በሚከናወነው ልዩ የንቅናቄ አጀንዳን ይፋ ማድረጉን እና ሂደቱንም መገምገሙን ያስታወሱት የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው፣ አጀንዳዎቹ ቀደም ባሉት ዓመታት እየተከናወኑ እንደ ከተማ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም በተምሳሌትነት የሚጠቀሱ ውጤቶችን ያስመዘገቡ እንደሆኑም ተናግረዋል፡፡

ከሰሞኑ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በ7 ቢሊዮን ብር ወጪ ግንባታው እየተከናወነ ያለውን የኢንዱስትሪ መንደር ጎብኝተው ነበር፡፡ በወቅቱ ካደረጉት ንግግር መካከል ቀጣዩን የፅሑፋችን መቋጫ አደረግነው “የህዝባችንን ጥያቄዎች የምንመልሰው የሚታዩ፣ የሚጨበጡ እና ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ በማተኮር ነው”፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

# ልማት የግብር መስታወት

- **የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከሐምሌ ወር 2017 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት 450 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ እየሰራ ይገኛል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

አመሻሽ ላይ ነው፤ በግምት 11 ሰዓት ገደማ ሆኗል፡፡ ለመጥለቅ እየዳዳች ካለችው ጀንበር የሚፈልቀው ብርቱካናማ ብርሃን በነፋሻማው የሲ.ኤም.ሲ ሰማይ ላይ ናኝቷል፡፡ በተለምዶ ሲ.ኤም.ሲ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ከመሪ ወደ ደራርቱ አደባባይ በሚወስደው መንገድ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ አባት ይራመዳሉ። በአግራሞት የመንገዱን ግራና ቀኝ ደጋግመው ያማትራሉ፡፡ ይህ መስመር የኮሪደር ልማት ከተከናወነባቸው የከተማዋ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ ቀላል የከተማ ባቡር ሐዲድ በሁለት የከፍለው አውራ ጎዳና በሁለቱም መስመር በአንድ ጊዜ ስድስት ተሽከርካሪዎችን ጎን ለጎን ያስኬዳል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
ከመገናኛ ወደ ሲኤምሲ በሚያመራው መስመር የተሰራ የኮሪደር ልማት ከፊል ገፅታ

የአውራ ጎዳናው ሁለቱም ጎን በእጅጉ ተውቧል፡፡ በቀይ እና አረንጓዴ ቀለማት ያሸበረቀው የብስክሌት መስመር፣ ሰፊው የእግረኛ መንገድ፣ የሳር ንጣፍና እፅዋት፣ የህንፃዎቹ የቀለም ቅብ፣ በአጭር ርቀት ልዩነት በአማሩ መቀመጫዎችና ደረጃዎች ተውበው የሚገኙ መናፈሻዎች፣ ዘመናዊነት የሚታይባቸው የታክሲ መጫኛና ማውረጃ ተርሚናሎች ለአካባቢው ልዩ ድባብ አላብሰውታል፡፡ ይህ የአካባቢው አዲስ ገፅታ በአቶ ነጋሽ ደበበ አንደበት እንዲህ ይገለፃል፡፡

አቶ ነጋሽ ደበበ ከመገናኛ ወደ ደራርቱ አደባባይ በሚወስደው መስመር ላይ የእግር ጉዞ የሚያደርጉት አግራሞት በተሞላበት አኳኋን የመንገዱን ግራና ቀኝ አብዝተው እያማተሩ ነው፡፡ ከሰላምታ ልውውጥ በኋላ፣ "ለአካባቢው እንግዳ ነዎት?" የሚል ጥያቄ በመሰንዘር ለውይይት ጋበዝኳቸው፡፡ ላለፉት 30 ዓመታት በዚሁ አካባቢ እንደኖሩና በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት አካባቢው የተጎናፀፈው ገፅታ ከጠበቁት በላይ እንደሆነባቸው አድናቆት በሚንፀባረቅበት አኳኋን ያወጉኝ ጀመር፡፡

የቀድሞውን ገፅታ እያስታወሱ ከአሁኑ ጋር አነፃፅረው ሲናገሩ፣ "በፊት የመኪናው መንገድ ጠባብ ነበር፡፡ እሱም ለባቡር ሐዲድ ተብሎ ተቀነሰ፡፡ በቂ የእግረኛ መንገድ አልነበረም፤ እርሱም ቢሆን በጎዳና ላይ ነጋዴዎች ተይዞ ስለነበር በእግር መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፤ ከዚሁ የተነሳ ሰው ከቤቱ ወጥቶ በእግር ለመንቀሳቀስ አይደፍርም፡፡ አሁን ከመንገዱ መስፋት ባለፈ አካባቢው ላይ የነበሩ አላስፈላጊ ግንባታዎች ተነስተው፣ አላግባብ የታጠሩ ክፍት ቦታዎችም አጥራቸው ተነቅሎ ግልፅና ክፍት የህዝብ መዝናኛዎች ሆነዋል፡፡ ይህም ከስጋት ነፃ የሆነ አካባቢ እንዲሆን አድርጓል። ወንጀል ተወግዷል። ሽፍንፍኑ ተገልጦ አሁን ሁሉም ነገር ፊት ለፊት የሚታይ ሆኗል፡፡" ሲሉ የተሰማቸውን ስሜት አጋርተውናል፡፡

ከአቶ ነጋሽ ጋር በነበረን አጭር ቆይታ ከአነሷቸው ነጥቦች መካከል "ከህዝብ የተሰበሰበ ግብር ተመልሶ ለህዝብ ጥቅም እየዋለ ነው፡፡ ይህ ዘመኔን በሙሉ ስመኘው የነበረ ጉዳይ ነው፡፡" በሚል መንደርደሪያ ትልቅ መልዕክት ያለው ቁም ነገር አጋርተውኛል፡፡

ሀሳባቸው ቃል በቃል ሲቀመጥ፣ "ደክሜ ከማገኘው ገቢ ለመንግስት የሚገባውን ግብር አስቀርቼ አላውቅም። ነገር ግን በዚህ ገቢ ህዝብን ታሳቢ ያደረጉ በቂ የልማት ስራዎች አይሰሩም የሚል ቅሬታ ነበረኝ፤ አሁን ቅሬታዬ በእርካታ ተተክቷል፡፡ ግብሩ በትክክልም መልሶ የግብር ከፋዮቹ መጠቀሚያ ሆኗል። ለዚህም ነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን የመሰለ መሻሻል በከተማዋ እየታየ ያለው።" ይላል፡፡

ይህም ለመሆኑ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የግብር አሰባሰብ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሰበሰበው ገቢና የልማት ስራው ትስስር በምን ሁኔታ ይገኛል? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ፅሑፍ ለማዘጋጀት አነሳሳኝ፡፡

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ካሉ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት አንዱ በሆነው ወረዳ 13 አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ግብር ከፋይ የሆኑት ወይዘሮ ስሜነሽ ግዛው የተባሉ አስተያየት ሰጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ የግብር አሰበሰብ ስርዓቱ እየዘመነና እየተሻሻለ መምጣቱን ጠቅሰዋል፡፡

አክለውም የግብር ከፋዩን ድካም የሚቀንሱና ጊዜን የሚቆጥቡ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሰራሮች በስፋት ተደራሽ መሆናቸው ጊዜአችንን በአግባቡ ለመጠቀምና ስራ ላይ አውለነው የተሻለ ገቢ ለማግኘት አስችሎናል ይላሉ፡፡

አሁን ላይ ወደ ግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መሄድ ሳይጠበቅባቸው በተንቀሳቃሽ ስልካቸው በአጭር የፅሑፍ ማሳወቂያ ተገልፆላቸው በሞባይል ባንኪንግ፣ በቴሌ ብር ወይም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚከፍሉበት አሰራር መመቻቸቱን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ከሚያጋጥሙ ችግሮች አንዱ የግብር አከፋፈሉ በባንክ የሚፈፀም ባለመሆኑ ግብር ለመክፈልም ሆነ ለማሳወቅ ረጅም ሰልፍና ምልልሶች እንደሚያጋጥሙ አንስተው፣ ይህን ችግር ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር በእጅጉ ጠቃሚ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በክፍለ ከተማው ወረዳ 3 የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋይ አቶ ፉአድ ቢላል በበኩላቸው፣ ግብርን በወቅቱና በአግባቡ መክፈል የዜግነት ግዴታ ብቻም ሳይሆን የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተሰማሩበት የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ሰርተው ከሚያገኙት ትርፍ ግብራቸውን በወቅቱና በአግባቡ ሲከፍሉ መቆየታቸውን አስረድተዋል፡፡

ዜጎች ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅርና ተቆርቋሪነት በተግባር ከሚያሳዩባቸው መገለጫዎች መካከል አንዱ ታማኝ ግብር ከፋይነታቸው ስለመሆኑ እሙን ነው። ግብርን በወቅቱና በአግባቡ መክፈል የዜግነት ግዴታ ብቻ ሳይሆን የስልጣኔ መገለጫም ነው፡፡ ዜጎች በፍቃደኝነት የሚከፍሉት ግብር ተመልሶ ለልማት ብሎም ለራስ ጥቅም የሚውል በመሆኑ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ያለማንም ጎትጓች የሚጠበቅበትን ግብር በወቅቱና በአግባቡ መክፈል እንዳለበት ይታመናል፡፡

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ ከድር ሲራጅ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ በክፍለ ከተማው ከ60 ሺህ የሚበልጡ ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል 25 ሺህ 522 ያህሎቹ ከንግድ ትርፍ ግብር የሚከፍሉ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

የአጠቃላይ የግብር ከፋይ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንደሚሄድ ያስታወሱት ስራ አስኪያጁ በክፍለ ከተማው በየዕለቱ አዳዲስ ንግድ ፍቃድ የሚያወጡ ደንበኞች መኖራቸውንና አሁን ላይ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮችን ጨምሮ 34 ሺህ 785 የአከራይ ተከራይ ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

እነዚህን ግብር ከፋዮች በአግባቡ ለማስተናገድ የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆኑንና በተለይ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የሚጠበቅባቸውን ግብር ማሳወቂያና የመክፈያ ጊዜ እንደመሆኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

እንደ አቶ ከድር ገለጻ፣ የሰው ኃይልን ጨምሮ የተለያዩ ግብዓቶችን ከማሟላት ጀምሮ ለውሳኔ ዝግጁ ማድረግና የተለያዩ መረጃዎችን የማደራጀት ብሎም ግብር የሚከፍሉና ያቋረጡትን የመለየት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በዝግጅት ምዕራፉ ትልቁ ትኩረት የነበረው ከወረዳ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ካለው የንግዱ ማህበረሰብ ጋር በተደረገ ውይይት የተነሱ ጥያቄዎች ናቸው ያሉት ስራ አስኪያጁ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በ90 ቀን እቅድ በማካተት ዝግጅት ተደርጓል፡፡

በታክስ አዋጁ እንደተቀመጠውም ደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 እንዲሁም ደረጃ 'ለ' ከሐምሌ 1 እስከ ጳጉሜ 6 የሚከፍሉ ሲሆን፣ በተለይም የጥቅምት ወር እንደ ከተማ ከፍተኛው ግብር የሚሰበሰብበት የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋዮች ግብራቸውን የሚያሳውቁበትና የሚከፍሉበት ወቅት ይሆናል፡፡

ለግብር ከፋዩ ማህበረሰብ የተሻለና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በየጊዜው ግንዛቤ ከማስጨበጥ ብሎም አዳዲስ አሰራሮችን በመተግበር ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ለመድፈን ጥረት ተደርጓል። የግብር ከፋዩን ድካም የሚቀንሱና ጊዜን የሚቆጥቡ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አሰራሮችን በስፋት ተደራሽ በማድረግ የውሳኔ አሰጣጡን ለማሳለጥ በትኩረት እየተሰራ ሲሆን፣ ባሉ የመክፈያ መንገዶች ያለምንም የሰው ንክኪ ክፍያቸውን እንዲፈፅሙ ተደርጓል፡፡

ከእነዚህም የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን ግብር ለማወቅና ለመክፈል ወደግብር ሰብሳቢው ተቋም በአካል ሳይሄዱ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው በአጭር የፅሑፍ ማሳወቂያ ተገልፆላቸው በሞባይል ባንኪንግ፣ በቴሌ ብር ወይም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚከፍሉበት አሰራር መመቻቸቱ ተጠቃሽ ነው፡፡

ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ በሐምሌና ነሐሴ ወር የተሻለ ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ እየሰራ ሲሆን፣ በእነዚህ ወቅቶች የ90 ቀናት እቅዱን ጨምሮ 450 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዷል፡፡ ከዚህም 238 ሚሊዮኑ ከደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች የሚሰበሰብ ነው፡፡ ቀሪው ከመደበኛ ወርሃዊ ገቢ፣ ከደመወዝና ከተለያዩ ገቢዎች የሚሰበሰብ መሆኑንና በሂደት ታይቶ ሊጨምር እንደሚችል ነው አቶ ከድር የሚገልፁት፡፡

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ አልማዝ መገርሳ በበኩላቸው፣ በወረዳው ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2017 ዓ.ም የግብር ግዴታቸውን መወጣት ያለባቸው 4 ሺህ 600 የሚጠጉ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች አሉ፡፡ እነዚህ ግብር ከፋዮች በተጠቀሰው ጊዜ እንዲከፍሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅስቀሳ ስራዎች መሰራታቸውን አስረድተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ከቅስቀሳ ስራው ጎን ለጎን በሐምሌ ወር የሚሰበሰበው የደረጃ 'ሐ' ግብር አሰባሰብ እንደከተማ ከወረደው የ90 ቀን እቅድ ጋር በማስተሳሰር እየተሰራ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ለዚህም የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቅቀው ወደ ስራ መግባቱን አስታውቀዋል፡፡

# “በሀሳብ ልውውጥ የሚመጣው ሰላም መሰረቱ ጠንካራ ነው”

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በጋዜጣዋ ሪፖርተር**

በድርድር፣ በመግባባት እና በሀሳብ ልውውጥ የሚመጣው ሰላም መሰረቱ ጠንካራ መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ያሉት ትላንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው በትግርኛ ቋንቋ ባስተላለፉት መልዕክት ነው፡፡ ሙሉውን መልዕክት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

እርቅ በሀገር ሽማግሌዎችና በኃይማኖት አባቶች መካከል የሚደረግ ምክክር ሲሆን ፍሬው ጣፋጭ ነው፡፡

የፌደራል መንግስት ችግሮችን በማጣራት በሽምግልና እና በውይይት ለመፍታት ቅድሚያ እንደሚሰጥ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተግባር አሳይቷል።

በሀገራችን የረዥም ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ እና የአስተዳደር ስርዓት “ብሔራዊ እርቅ፣ ብሔራዊ ምክክር፣ የፖለቲካ ውይይት” ወዘተ ... እነዚህን ማህበራዊ ጽንሰ ሃሳቦች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በይፋ ያስተዋወቀው ይህ መንግስት ብቻ ነው ቢባል ግልፅ ሃቅ ነው።

“ትርምስ በረከትን ያርቃል” እንደሚባለው ትርምስ ትርምስን ይፈጥራል፣ ግጭት ግጭትን ይፈጥራል እናም በችግር ከበባ ውስጥ እንድንኖር ያደርገናል፤ በረከትንም፣ ሰላምንም ሊያመጣ አይችልም። በታሪካችን ዘላቂ ሰላም በግጭት እና በጦርነት አልመጣም፤ ሊመጣ አይችልም። በአንፃሩ በድርድር፣ በመግባባት እና በሀሳብ ልውውጥ የሚመጣው ሰላም መሰረቱ ጠንካራ ነው።

በዚህ ረገድ ከትግራይ የተውጣጡ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላት ጋር ለቀጣይ መድረኮች እድል የሚከፍት ጥልቅ ውይይት አካሂደናል። በውይይታችንም በርካታ ጉዳዮች ተነስተው ተመካክረንባቸዋል፡፡ በተለይም የተፈናቃዮች ጉዳይ፣ የትግራይ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በዋናነት ምክክር የተደረገባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ነበሩ፡፡

በፐብሊክ ዲፕሎማሲው አባላት በኩል በርካታ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን፣ መንግስት ከህዝቡ ጋር ተቀራርቦ መስራት እና ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀቱን ሊቀጥል ይገባል የሚሉትን ጨምሮ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዋል።

በፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት አተገባበር ላይ ያሉ ድክመቶችን እንዴት ማረም እንደሚቻል እና የቃላት አጠቃቀሞችን እንዲሁም አልፎ አልፎ ወደ ግጭት ሊያመሩ የሚችሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል እና ትግራይ ከጦርነት ቁስሎች እንድትታከም ብሎም ወደ መደበኛ ህይወት እንድትመለስ በጥልቀት ተወያይተናል።



ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

የትግራይ ተወላጆች እና የትግራይ ምሁራን በሀገራቸው ኢትዮጵያ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ውስጥ በስፋት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን መፍጠር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ካነሳናቸው እና ከተስማማንባቸው ነጥቦች መካከል ይገኙበታል፡፡

የፌዴራል መንግስት የትግራይ ፖለቲካ፣ ጸጥታና ኢኮኖሚ ወደ ቀድሞ ሁኔታው የሚመለስበትን ሁኔታ ለመፍጠር ከህዝቡ፣ ከጊዜያዊ አስተዳደር መንግስት እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀራርቦ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አረጋግጥላችኃለው።

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ !

## ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር፡- 001/2018 ዓ.ም

የአ/ቃ/ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል የመንግስት ግዥ ቡድን ለሴክተሮች የሚያሰፈልጉ የአገልግሎት ግዥዎች /የህትመት ሥራዎች፤ የመኪና ኪራይ፤ የድንኳን እና ዲኮር አገልግሎቶች፤ የመስተንግዶ ግዥዎች እና የዋንጫዎች/ ግዥ በግል ፅጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1፡- የህትመት ሥራዎች፤
ሎት 2፡- የመኪና ኪራይ፤
ሎት3፡- የድንኳን እና ዲኮር አገልግሎቶች፤
ሎት4፡- የመስተንግዶ ግዥዎች፤
ሎት5፡- የዋንጫዎች ግዥ፤
ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል፡፡

1. በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ
2. የንግድ ምዝገባ ፍቃድ ያለው
3. የዘመን ግብር የከፈሉና በአቅራቢነት የተመዘገቡ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ
5. የጨረታ ማስከበሪያ CPO

ሎት፡-1፡- 20,000.00 / ሃያ ሺ ብር ብቻ/
ሎት 2፡- 40,000.00 / አርባ ሺ ብር ብቻ/
ሎት3፡- 40,000.00 / አርባ ሺ ብር ብቻ/
ሎት4፡- 20,000.00 / ሃያ ሺ ብር ብቻ/
ሎት5፡- 10,000.00 / አስር ሺ ብር ብቻ/

ሲፒኦ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት በሚል ያሰራሉ፡፡
ተጫራቾች የማይመለስ 200.00 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛ ለሚወዳደሩ ተጫራቾች በሀገር ዉስጥ ምርት ላይ ብቻ የተሳተፉ እና ካደራጃቸው አካል ስድስት ወር ያልሞላዉ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ በነፃ መውሰድ የሚችሉ ሲሆን ይህ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል የመንግስት ግዢ አስተዳደር ቡድን ሁለተኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡

6. የአሸናፊዉ ድርጅት CPO ተመላሽ የሚሆነዉ የዉል ማስከበሪያ የአጠቃላይ ያሸነፈበትን ዋጋ 10% ሲያሲዝ ብቻ ነዉ፡፡
7. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ ከመስሪያ ቤቱ በገዙት ዋጋ ማቅረቢያ ብቻ በግልጽ እና በሚታይ መልኩ ያለስርዝ ድልዝ በመሙላት ኦርጅናል እና ፎቶ ኮፒውን በተለያየ ፖስታ በማሸግ ሁለት ፖስታ በአንድ ላይ በታሸገ ኤንቨሎፕ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር (10) የሥራ ቀናት እስከ 11፡30 ሰዓት ሰነዱን መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
8. በአስራ አንደኛው (11) የስራ ቀን ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 4፡00 ሰዓት ተጫራጮች ሰነድ በማስገባት 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ ልክ 4፡30 ባለቤቱ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሁለተኛ ፎቅ ጨረታው ይከፈታል፡፡
9. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡- አድራሻ ከቃሊቲ መናኸሪያ ፊት ለፊት ባለው የአስተዳደር ህንፃ ላይ ሁለተኛ ፎቅ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ፑል የመንግስት ግዢ አስተዳደር ቡድን**

# የአረንጓዴ ሽፋኑ መጨመር አንድምታ

- ችግኝ በመትከል የመዲናዋን የአረንጓዴ ሽፋን ማሳደግ ላይ የተሰሩ ስራዎች ከስም ባሻገር የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን የሚያስመሰክሩ ናቸው

**በስንታየሁ ምትኩ**

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ህዝብ በስፋት እየተሳተፈባቸው ከሚገኙ ስራዎች መካከል በቀዳሚነት ይቀመጣል። በመርሀ ግብሩ የዕድሜ፣ የፆታ፣ የሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች ሳይስተዋሉ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በአንድነት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

ወይዘሮ ሪታ ፈቃዱ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 በተለምዶ ድል በር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ ከተጀመረ አንስቶ ባለፉት ዓመታት በተከታታይ ችግኝ በመትከል ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ዛፍ የሰው ልጅ ለመኖር እጅግ አስፈላጊ የሆነው አክሲጂን ምንጭ ነው። እያጋጠመ ያለውን ከፍተኛ ሙቀት፣ ድርቅ፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና የጎርፍ አደጋዎችን ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡ ከምንም በላይ ጥቅሙ "ለራሴ፣ ለከተማዬና ለሀገሬ ነው" በሚል መነሻ ችግኝ በመትከል እየተሳተፉ እንደሆነ ወ/ሮ ሪታ ይናገራሉ፡፡

ባለፉት ዓመታት ከመቀጠያ እስከ እንጦጦ ማርያም ባለው አካባቢ ችግኞችን ተክለዋል፡፡ በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢያቸው ውስጥ ባላቸው አነስተኛ ቦታም ባለፈው ዓመት ፅድ እና ለምግብነት የሚውሉ እንደ አቦካዶና አፕል ያሉ የፍራፍሬ ችግኞችን ተክለዋል። እነዚህ ችግኞች ሲወጡ እና ሲገቡ ሲመለከቷቸው ለዓይናቸው ተስፋና ደስታን እየፈጠረላቸው ይገኛል። ችግኞቹ ሲያድጉም እንደ ጥላ በመሆን ከፀሐይ ሀሩር መከላከያ እንዲሁም ለምግብነት እንደሚውሉም ተናግረዋል፡፡

ዘንድሮም ወይዘሮ ሪታ ወደ እንጦጦ መውጫ አርሴማ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኝ ስፍራ ላይ አሻራቸውን አኑረዋል፡፡ በችግኝ ተከላ ላይ ሲሳተፉም ከፍተኛ ደስታና እርካታ እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል፡፡ "ችግኝ ስተክል ውስጤን በጣም ደስ ይለዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ለከተማና ለሀገር ጥቅም ከፍተኛ ትርጉም ያለውን አሻራ በማሳረፍ የራሴን ድርሻ እየተወጣሁ እንደሆነ ይሰማኛል" ይላሉ፡፡

ችግኝ ከመትከል ባሻገር የተተከሉት እንዲፀድቁ በሚሰሩበት የጉለሌ ክፍለ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ጽህፈት ቤት በኩል በየጊዜው ውሃ በማጠጣት ክትትል እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

አቶ አዳሙ ዘገየ ሌላኛው በአረንጓዴ ዐሻራ ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉት መካከል ናቸው፡፡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በተለምዶ ጨረታ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ አዳሙ፣ ከዚህ ቀደም የምኖርበት አካባቢ በደን የተሸፈነ፣ ንፁህ ወንዞችና ጅረቶች ኩልል እያሉ የሚፈሱበት ነበር፡፡ ከነዋሪው ቁጥር መጨመርና አዳዲስ ሰፈሮች መመስረት ጋር ተያይዞ የደንና አረንጓዴ ሽፋኑ እየተመናመነ ሲመጣ ይህንን ለማስተካከል የበኩሌን ድርሻ ለመወጣት




ፎቶ ከፋይል

አዲስ አበባ የምትተክለው የችግኝ መጠን ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል

ችግኝ ወደ መትከልና መንከባከብ ገባሁ ይላሉ፡፡

አቶ አዳሙ በሚኖሩበት ወረዳ የአረንጓዴ ልማት አምባሳደር ናቸው። እስከአሁንም በጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል፣ እንጦጦ ጫካና በአካባቢያቸው በተለያዩ ስፍራዎች ጉድጓድ በመቆፈርና ችግኝ በመትከል ተሳትፈዋል፡፡ በሰፈር የተለያዩ ዕድሮች አመራር እንደመሆናቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ማህበረሰቡ ችግኝ እንዲተክልና እንዲንከባከብ ግንዛቤ በመፍጠርና በማስተባበር እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

"ችግኝ መትከልና መንከባከብ ያስደስተኛል፡፡ ችግኝ የህልውና መሰረት ነው፡፡ ምግብ፣ ልብስ፣ ጥላ እና ውበት ነው፡፡" የሚሉት አቶ አዳሙ እሳቸውን ጨምሮ ማህበረሰቡ በሚያደርገው ተሳትፎ በሰፈራቸው ንፁህና አረንጓዴ አካባቢዎች እየተፈጠሩ ነው፡፡ ለአብነትም በወረዳ 5 ክልል ውስጥ የሚገኘው አወሊያ የሙስሊም ትምህርት ቤት እና በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ስር በሚገኘው ቅዱስ ፍራንቺስኮ ገዳም አካባቢ የቆሻሻ መጣያ የነበሩ ስፍራዎች፣ በአግባቡ ታጥረው ችግኝ ተተክሎባቸው ውብ፣ ጽዱና አረንጓዴ ሆነዋል፡፡ በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብርም በግላቸው እስከ 200 ችግኞች ለመትከል ማቀዳቸውን ነግረውናል።

## አዲስ አበባ እና አረንጓዴ ዐሻራ

በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ እያስከተለ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል፣ የምግብ ዋስትናን እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በ2011 ዓ.ም ተጀምሮ ባለፉት ስድስት ዓመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ40 ቢሊዮን በላይ ችግኝ ተተክሏል፡፡

በአዲስ አበባም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከተጀመረበት አንስቶ ባለፉት ዓመታት በየዓመቱ በከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎ በሚሊዮን የሚቆጠር ችግኝ እየተተከለ ነው፡፡ በ2011 ዓ.ም 6 ሚሊዮን፣ በ2012 ዓ.ም ከ8 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ፣ በ2013 ዓ.ም ከ11 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ፣ በ2014 ዓ.ም ከ14 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ፣ በ2015 ዓ.ም ከ17 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ እንዲሁም በ2016 ዓ.ም ከ27 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ችግኝ ተተክሏል፡፡ ባለፉት ስድስት ዓመታት በድምሩ 85 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በአዲስ አበባ በ2017 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከ4 ነጥብ 2 ሚሊየን በላይ ችግኝ ለመትከል ዕቅድ ተይዟል፡፡

በአዲስ አበባ ደረጃ የ2017 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብርን ባስጀመሩበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፣ ባለፉት ስድስት ዓመታት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር አማካኝነት የከተማዋ የአረንጓዴ ሽፋን ከ2 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 22 በመቶ ማደግ ችሏል፡፡ ከተተከሉት ውስጥም ከ85 በመቶ በላይ የሚሆኑት ችግኞች ፀድቀዋል፡፡

## አረንጓዴ አሻራ ለመዲናዋ የሚያስገኘው ትሩፋት

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2017 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፣ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ለኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶችን እያመጣ ይገኛል፡፡ አረንጓዴ ዐሻራው ኢኮኖሚውን እያነቃቃ ነው፡፡ ቱሪዝምን ብናነሳ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት አንድም ውብ የሆነውን መልክዓ ምድሯን ለማየት እና ንጹህ፣ ምቹና ተስማሚ በሆነው የአየር ንብረቷ በመማረክ ነው። በኮንፈረንስ ቱሪዝም ማዕከልነት ኢትዮጵያ ተመራጭ እንድትሆን አረንጓዴ ዐሻራ የማይተካ ሚና ተጫውቷል፡፡ በተያዘው ዓመትም ከ100 በላይ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄዳቸውን ለማሳያነት አንስተዋል፡፡

ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያም አዲስ አበባ እንደሀገር ከተገኘው ትሩፋት ምን ያህል ተጠቃሚ እየሆነች እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ በከተማዋ ባለፉት ዓመታት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ደርቀው የነበሩ ወንዞችና ጅረቶች ፍሰት ጎልብቷል፤ ጠፍተው የነበሩ ምንጮች መፍለቅ ጀምረዋል። በአፈርና ስነ ምህዳር ጥበቃ ትላልቅ ለውጦች መታየት ጀምረዋል፡፡ የተተከሉ ችግኞች ጥላ፣ ውበት፣ የቱሪስት መስህብ፣ ምግብ በመሆን እንዲሁም የስራ ዕድልና ገቢ በማስገኘት የሚታይና የሚጨበጥ ለውጥ መጥቷል፡፡

የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በሆርቲካልቸር፣ ሁለተኛ ድግሪያቸውን ደግሞ በአካባቢ የአየር ንብረት አስተዳደር ዘርፍ ያጠኑትና በጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል የሆርቲካልቸር ልማት ዳይሬክተር አቶ መክብብ ማሞም ይህንን ይጋሩታል፡፡

አዲስ አበባ የኢትዮጵያውያን መዲና ብቻ ሳትሆን የአፍሪካና የዓለም የዲፕሎማሲ ከተማ ናት፡፡ ችግኝ በመትከል የአረንጓዴ ሽፋኗን ማሳደግ ላይ የተሰሩ ስራዎች ከስም ባሻገር የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን የሚያስመሰክሩ ናቸው፡፡ በችግኝ ተከላው በአረንጓዴ የተሸፈነ ምቹና ሳቢ የስራና የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር ተችሏል። ተራራማ አካባቢዎች፣ መሀል ከተማ፣ መዝናኛ ስፍራዎች፣ የመንገድ አካፋዮችና ክፍት ቦታዎች አረንጓዴ በመልበሳቸው ሙቀትን በመቀነስ ሚዛኑን የጠበቀ የአየር ንብረት እንዲኖር አዎንታዊ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ችግኞች በተተከሉ ቁጥር ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን ካርቦንዳይኦክሳይድ ዕፅዋቶች ስለሚጠቀሙት የሙቀት አማቂ ጋዞች ክምችት እንዲቀንስ ያደርጋሉ፡፡ በሀገር ደረጃ ካሉ ተሸከርካሪዎች አብዛኞቹ በአዲስ አበባ የሚገኙ ናቸው፡፡ የዕፅዋት ሽፋን ማደግ ማለት ከተሽከርካሪዎች የሚወጣና ወደከባቢ አየር የሚለቀቅ ጋዝ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የከተማ ግብርናው እንዲጠናከር ምን እየተሰራ ነው?

በሰገነት አስማማው

በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ የከተማ ግብርና ዘርፍ አንድ አማራጭ ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም በርካታ ነዋሪዎች በዶሮና በወተት ላም እርባታ፣ በከብት ማድለብ፣ በንብ ማነብ፣ በሰብል እና በሌሎችም ዘርፎች ተደራጅተው በመስራት ውጤታማ እየሆኑ መጥተዋል። ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ፣ ትምህርት ቤትን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማት የጓሮ አትክልቶችን በመትከል የምግብ ፍጆታቸውን እየሸፈኑ አለፍ ሲልም ገቢ እያገኙና የስራ ዕድል እየፈጠሩ ነው፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በከተማ ግብርና ዘርፍ የተሰማሩት አርሶ አደር ናትናኤል ባጫ ቀድሞ ጤፍ፣ ሽምብራ፣ ጓያ በማምረት ኑሯቸውን ሲመሩ ቆይተዋል። በተጨማሪነት በምን መልክ ቢሰሩ የተሻለ ውጤት ማምጣት እንዳለባቸው ባለማወቃቸው የሚፈለገውን ምርት ማግኘት እንዳልቻሉ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

በወረዳው በከተማ ግብርና ባለሙያዎች ግንዛቤ ከተሰጣቸው በኋላ በስራቸው ውጤታማ መሆን፣ ገቢያቸውም እያደገ መምጣቱን አልሸሸጉም፡፡ ባገኙት ግንዛቤ በጓሮ አትክልት ዘርፍ ከ2013 ዓ.ም አንስቶ የሀበሻ ጎመን፣ ቆስጣ፣ ጥቅል ጎመን፣ ሰላጣ በማምረት ከእለት ጉርስ አልፎ ለገበያ በማቅረብ ገቢ ያገኛሉ፡፡ በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በ8 ሺህ ብር ካፒታል የተጀመረው የጓሮ አትክልት ስራ 900 ሺህ ብር ካፒታል አፍርቶላቸዋል፡፡ ቀድሞ በአንድ ክፍል ቤት ባልተመቻቸ ሁኔታ ይኖሩ የነበረው አሁን አራት ክፍሎች ያለው የተሻለ መኖሪያ ቤት መስራትም ችለዋል፡፡

አርሶ አደሩ የከተማ ግብርና ስራን ከማጠናከር ጎን ለጎን በ2014 ዓ.ም ስንዴን ወደ ማምረት ተሸጋገሩ፡፡ በ1 ነጥብ 5 ሄክታር መሬት ላይ በ25 ሺህ ብር ካፒታል የጀመሩት የስንዴ ማምረት ስራ አሁን ላይ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያ፣ የአረም ማጥፊያ መድኃኒት መግዢያን ችሎ 70 ሺህ ብር ካፒታል ማፍራት ችለዋል፡፡ በጓሮ አትክልቱ ለ3 ዜጎች ቋሚ እና ለ5 ጊዜያዊ እንዲሁም በስንዴው ስራ ለ3 ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡

"የከተማ ግብርና ባለሙያዎች የስራ ቦታዬ ድረስ በመምጣት ስንዴን በመስመር እንዴት መዝራት እንዳለብኝ በሃሳብም፤ በተግባርም አሳይተውኛል። ማዳበሪያ በወረዳ ደረጃ በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርብልናል፡፡ በዚህም በከተማ ግብርና ዘርፍ በመስራቴ ውጤታማ እየሆንኩ እገኛለሁ፡፡ በቀጣይም ስራዬን አሻሽዬ በመስራት ለሌሎች ዜጎች ተጨማሪ የሥራ እድል የመፍጠር እንዲሁም በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች በዘርፉ ቢሰማሩ ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የመስራት እቅድ አለኝ" ብለዋል፤ አርሶ አደር ናትናኤል፡፡




ግራፊክስ በዳንኤል ተስፋይ
በከተማ ግብርና ተሳትፈው ተጠቃሚ ከሆኑ ነዋሪዎች ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ቁጥራዊ መረጃ

ባለሙያዎች ግንዛቤ በመስጠት ረገድ ድጋፍ እንዳደረጉላቸው የሚያስታውሱት አርሶ አደሩ፣ "ማምረት ከጀመርኩ በኋላ ያየኝ ባለሙያ የለም፡፡ ውጤቴን ቢያዩ የበለጠ እበረታታለሁ" ሲሉ የድጋፍ ስራው ቀጣይነት ባለው መልኩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ ከአርሶ አደር ቤተሰብ የወጡት ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ ሀሰን በሽር በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 በከተማ ግብርና ዘርፍ እየሰሩ ይገኛሉ። ከቤተሰባቸው ባገኙት ልምድ በ2008 ዓ.ም በወተት ላም እርባታ ላይ ተሰማሩ። በአንድ የወተት ላም የተጀመረው ስራ አሁን ላይ 25 የወተት ላሞች ደርሰዋል። በቀን 250 ሊትር ወተት ለሽያጭ ማቅረብ፣ ለ10 ዜጎችም የሥራ እድል መፍጠር ችለዋል፡፡

አቶ ሀሰን የከተማ ግብርና ውጤታማ እያደረጋቸው መሆኑን፣ "ጠንክሬ በመስራቴ ልጆቼን ማስተማርና ቤተሰቤን በተገቢው ማስተዳደር ችያለሁ፡፡ ለመኖሪያ ቤት እና ለስራ የሚሆን አንድ ፒክ አፕ መኪና ሀብት ማፍራት ችያለሁ። 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ካፒታልም አፍርቻለሁ" ሲሉ ገልፀዋል፡፡ የከተማ ግብርና ባለሙያዎች በሚሰሩት ስራ ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉላቸው ቢሆንም የመኖ ዋጋ መናር ስራቸውን በአግባቡ ለመስራት እንቅፋት እንደሆነባቸውም አክለዋል፡፡

## ኮሚሽኑ በዘርፉ ለተሰማሩት ምን ድጋፍ እያደረገ ነው?

የዝግጅት ክፍላችን በከተማ ግብርና በተለይ በእንስሳት እና ዕፅዋት ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ምን ድጋፍ እያደረገ ነው ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽንን ጠይቋል፡፡ በኮሚሽኑ የእንስሳት እርባታ ባለሙያ አቶ ቢኒያም አድማሱ በሰጡት መረጃ፤ በዋናነት በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ዜጎች በአካል በመሄድ የድጋፍና ክትትል እንዲሁም የማማከር ሙያዊ ስራ ይሰራል። በወተት ላም፣ በዶሮ፣ በዓሳ፣ በንብ ማነብ፣ በከብት ማድለብ ላይ እንዴት መስራት እንዳለባቸው፣ በምን ሁኔታ ቢሰሩ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ወረዳ ድረስ በመውረድ ይሰጣቸዋል፤ ለስራቸው አጋዥ የሆነ መረጃ በበራሪ ወረቀት መልክ በማዘጋጀትም እንዲሁ፡፡ የአመጋገብ፣ የውሃ አጠቃቀም፣ ግብአት ላይ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ስልጠናም ይሰጣል፡፡

ባለሙያው እንዳስረዱት፤ ለአርሶ አደሮች በማዕከል ባሉ ባለሙያዎች ከሚሰጠው የማማከርና ድጋፍ ስራ ባለፈ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ ደረጃ ባሉ ባለሙያዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ

ወደ ገጽ 19 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### ግብር ከፋዮች ሊይዟቸው የሚገቡ የሒሳብ ሰነዶች

ግብር ከፋዮች የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚደረግበት ዓላማ በትክክለኛ መረጃ ላይ በመመስረት ግብር ለማስከፈል እና የታክስ ተመላሽን ለመፍቀድ ነው፡፡ ስለሆነም መያዝ ከሚኖርባቸው የሂሳብ ሰነዶች መካከል፡-

ከንግድ ስራው ጋር በተገናኘ በየቀኑ የሚያገኘውን ማንኛውም ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤

- ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብን የተከተለ የሂሳብ ሰነድ፤

ህጋዊ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ፤

- የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ፤
- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፤
- በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ማከመቻ መሳሪያ ውስጥ ተከማችቶ የተያዘ፤
- ከግብር ከፋዩ ቅድመ ታክስ ተቀናሽ የተደረገበትን የታክስ መጠን ደረሰኝ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ምንጭ፡- የገቢዎች ሚኒስቴር

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ 1183/2012

**ኤሚሊያ ፍሬድሪክ (ዐቃቤ ሕግ)**

የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 በአስተዳደር ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሥልጣን በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲያውሉ እና በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ብቻ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ነው። አዋጁ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያው የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ በሚመለከት ተቋማት ምን ቅድመ ሁኔታዎችን መከተል አለባቸው የሚለውን ያስቀምጣል፡፡ ሁለተኛው በህግ መመሪያ ያወጡት ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት መመሪያ ሲያወጡ መከተል ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር ያስቀምጣል ሦስተኛው የአስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍርድ ቤት ስለሚኖራቸው ክለሳ የሚዳስስ ይሆናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ስንመለከት አስተዳደራዊ ውሳኔ ምን ማለት ነው? የሚለውን እናነሳለን አስተዳደራዊ ውሳኔን አዋጁ ትርጉም ሲሰጠው “አስተዳደራዊ ውሳኔ ማለት መመሪያ ማውጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ነው” በማለት ያስቀምጣል፡፡

“የአስተዳደር ተቋማት ምንድን ናቸው?” የሚለውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የአስተዳደር ተቋም ማለት አንድን የተለየ ሕግ ለማስፈጸም ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል ነው በማለት ያስቀምጣል፡፡ የአስተዳደር ተቋም በህግ አፈፃፀም ሥር የሚገኝ ተቋም ሆኖ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም ሥልጣን በሕግ የተሰጠው አካል ነው፡፡ የአስተዳደር አካላትን ስንመለከት ሁለት አይነት የአስተዳደር አካላት አሉ፡፡

የመጀመሪያው በአስፈፃሚው ሥር የሚቋቋም የአስተዳደር ተቋም ሲሆን፤ ሁለተኛው ከአስፈጻሚ አካል ውጪ የሚቋቋም የአስተዳደር ተቋም ነው፡፡

በአስፈፃሚው አካል ሥር የሚቋቋመው የአስተዳደር ተቋም ተጠሪነቱ ለአስፈፃሚው ሲሆን የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሾመው በአስፈጻሚው አካል የበላይ ኃላፊ ነው፡፡ ከአስፈፃሚው አካል ውጪ የሚቋቋመው የአስተዳደር ተቋም የበላይ ኃላፊ የሚሾመው በአስፈፃሚው አካል የበላይ ኃላፊ አቅራቢነት በህግ አውጪው የሚሾም ይሆናል፡፡

በአዋጁ ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ አቀራረብን በሚመለከት ያስቀመጣቸውን ነጥቦች ስንመለከት፤ የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰው ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የሚቀርበው ጥያቄ በጽሑፍ ብቻ መሆን እንዳለበት አዋጁ ያስቀምጣል፡፡ ይህም ማለት በቃል የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። በጽሑፍ የሚቀርበው ጥያቄ በአካል ሊሆን ይችላል፡፡ ካልሆነም በማንኛውም በተመዘገበ ፖስታ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መንገድ መቅረብ ይችላል፡፡ ሌላው አቤቱታውን የተቀበለው የአስተዳደር ተቋም አቤቱታውን መዝግቦ ስለ መቀበሉ የጽሑፍ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። የአስተዳደር ተቋማት አቤቱታውን ከተቀበሉ በኋላ ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ አዋጁ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች መከተል እንዳለባቸው አዋጁ ይደነግጋል፡፡

እነኝህም መርሆዎች የአስተዳደር ውሳኔ መስጠት የሚችለው ሥልጣን የተሰጠው የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ብቻ መሆን አለበት፡፡

ውሳኔ ሲሰጥ መከተል ያለበት ለአስተዳደር ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መሆን አለበት፡፡ ሌላው የአስተዳደር ተቋሙን ተገልጋይ የግል ጥቅም እና በአስተዳደር ተቋሙ ዓላማ የተመለከተውን የሕዝብ ጥቅም ማመዛዘን፤ የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር፣ ትጋት እና ጥንቃቄ ማክበር አለበት፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው ጉዳይ ወይም ፍላጎት መመራት የለበትም። የአስተዳደር ውሳኔ ከመስጠቱ በፊትም የሚመለከተውን ሰው ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በሚገባ ማዳመጥ እና መመርመር እንደነገሩ ሁኔታ የሦስተኛ ወገን ተቃዋሚን እና የሕዝብን አስተያየት ማዳመጥ እና በቅን ልቦና በቂ ምክንያት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ሁሉንም ተገልጋዮች በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት መጠን፣ በትውልድ ሁኔታ ወይም በሌላ ምክንያት ልዩነት ሳያደርግ መወሰን አለበት፡፡ ከተገልጋዩ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ ጉዳዩን ከማየት እራሱን ማግለል አለበት። የአስተዳደር ውሳኔውን ሳይዘገይ በተገቢው ጊዜ መስጠት እና በጉዳዩ ዙሪያ ያሉ ጥቅሞች በውሳኔው መዘግየት ምክንያት ለጉዳት እንዳይጋለጡ ማድረግ አለበት፡፡

2. በአዋጁ ላይ ከተቀመጡ ጉዳዮች የአስተዳደር ተቋማት የመመሪያ አወጣጥ ሥነ ሥርዓትን ይሆናል።

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በህግ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሰረት መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡ መመሪያው እንዲወጣ በዋናው ህግ ላይ የተቀመጠ ሲሆን የአስተዳደር ተቋሙ በ90 ቀን ውስጥ ማውጣት እንዳለበት ተቀምጧል። በዋናው ህግ ላይ በአስገዳጅ ሁኔታ ያልተቀመጠ እንደሆነ መመሪያው እንዲወጣ በተጠየቀ ጊዜ በተገቢ ጊዜ ውስጥ መመሪያ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ስንመለከት አንድ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት መጀመሪያ መዝገብ ማደራጀት ያስፈልገዋል፡፡ መዝገብ ማደራጀት የሚያካትታቸው የመመሪያውን ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ፤ የመመሪያ አወጣጥ ድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለበት፡፡ ሁለተኛው ማስታወቂያ ማውጣት ሲሆን የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት ስለሚያወጣው ረቂቅ መመሪያ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና የተቋሙን ድረ ገጽ ጨምሮ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡

ሦስተኛው የሚወጣውን ረቂቅ መመሪያ ለአስተያየት ለሚመለከታቸው አካላት እና ለባለድርሻ አካላት መላክ አለበት፡፡

አራተኛው የውይይት መድረክ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱ ቅድመ ሁኔታዎችን አንዳንድ መመሪያዎች ሊከተሉ እንደማይገባ በልዩ ሁኔታ መመሪያዎች ሊወጡ እንደሚችሉ በአዋጁ ላይ ተቀምጧል፡፡ እነዚህም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በመኖሩ በግዴታዎቹ ሥርዓት ውስጥ ለማለፍ ጊዜ የማይፈቅድ ሲሆን፤ ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የመመሪያውን ተፈጻሚነት ፋይዳ ቢስ የሚያደርግ ሲሆን፤ ከላይ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ሳይከተል መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

አምስተኛ ከላይ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ከጨረሰ በኋላ የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያውን ያፀድቃል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት መመሪያው በአስተዳደር ተቋሙ መጽደቁ ብቻ መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆን አያደርገውም፡፡ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ እንደወጣ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡ ፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የተላከለትን መመሪያ ቁጥር ሰጥቶ ይመዘግባል። መመሪያው ስለመመዝገቡም ለአስተዳደር ተቋሙ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የመዘገበውን መመሪያ በድህረ ገጹ ላይ መጫን አለበት፡፡ የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሠራጨት እና በተቋሙ ድህረ ገጽ ላይ መጫን አለበት፡፡

3. በአዋጁ ላይ ከተቀመጡ ጉዳዮች በፍርድ ቤት በአስተዳደር መመሪያዎች እና ውሳኔዎች ላይ ስለሚኖር ክለሳ ይሆናል። ማንኛውም ሰው የአስተዳደር መመሪያ እና ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል። ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል።



# እፎይታን ... ከገጽ 1 የዞረ

በወቅቱ ስለበሽታው ባህርይ ያለው እውቀት አናሳ በመሆኑ፣ የመጀመሪያውን የኩላሊት እጥበት ህክምና ካገኘ በኋላ በቀላሉ ተሽሎት ወደ ቤት እንደሚመለስና እስከመጨረሻው እንደሚድን ያስብ ነበር። ይሁን እንጂ ህክምናው ቀጣይነት ያለው ክትትል እንደሚፈልግ ቆይቶ እንደተረዳ ይናገራል፡፡

ህመሙ ያጋጠመው በአንድ የኢንሹራስ ኩባንያ በክለርክ ባለሙያነት ተቀጥሮ ብዙ ሳይቆይ በመሆኑ የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ መሆን አልቻለም። በዚህም ምክንያት ለኩላሊት እጥበት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት ሲፈተን መቆየቱን ያስረዳል፡፡

ወጣት ስዩም በግሉ ህክምናውን ለመውሰድ የኢኮኖሚ አቅሙን ስለፈተነው ቅናሽ ፍለጋ አሉ የተባሉ የህክምና ተቋማትን ሁሉ ዞሯል፡፡ ህክምናውን ሲጀምርም ለአንድ ጊዜ የኩላሊት እጥበት ህክምና 3 ሺህ ብር ይከፍል ነበር፡፡ ሶስት ጊዜ ሲወስድ በሳምንት የሚከፍለው ገንዘብ 9 ሺህ ብር ይሆናል፡፡

የህክምና ወጪው እየፈተነው ሲመጣ በሳምንት ሶስት ጊዜ የሚያደርገውን ወደ ሁለት ዝቅ እንዲል አደረገ፡፡ ከዚያም አለፍ ሲል የተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጾችን (ፌስቡክ እና ዩትዩብ) በመጠቀም ማህበረሰቡ ድጋፍ እንዲያደርግለት በመጠየቅ በሚያገኘው ገንዘብ ህክምናውን ሲወስድ መቆየቱን ይናገራል።

"የኩላሊት እጥበት ህክምና ለማግኘት ሳወጣ የነበረው ወጪ ከፍተኛ ነው። ህክምናውን አግኝቼ ህይወቴ መቀጠል ስለነበረበት ቤተሰቤ ያላቸውን መኖሪያ ቤት ሸጠዋል፡፡ ቤታችን ከተሸጠ በኋላም ያለው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ አልቆ ነበር፡፡ " ሲል የህክምና ወጪው ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ ወጣት ስዩም ይናገራል፡፡

ቤተሰቡ ጭምር ያላቸውን ሀብት አሟጥጠው ችግር ውስጥ በወደቁበት ወቅት፣ ከሁለት ዓመት በፊት በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በነፃ የኩላሊት እጥበት ህክምና ዕድል አገኘ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በማዕከሉ ህክምና እያገኘ ነው፡፡ ይህም "ከምንም በላይ ተረጋግቼ እንድኖር አግዞኛል፡፡ ሰኞ የኩላሊት እጥበት ህክምና ካገኘን በኋላ ቀጥሎ ያሳስበን የነበረው ስለጤናችን ሳይሆን ለረቡዕ የሚሆን የህክምና ገንዘብ ከየት እናገኛለን የሚለው ነው፡፡ ገንዘብ የምናገኝበት መንገድ በጣም ፈታኝ ስለነበር፤ ጭንቀት ውስጥ እንገባለን፡፡ እርዳታ ጠይቀንም የማናገኝባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡" ሲል ነበር ህክምናውን በነጻ ማግኘቱ ትልቅ እፎይታ እንደሰጠው የሚያስረዳው፡፡

በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚሰጠው ነፃ የኩላሊት እጥበት ህክምና እንደ ወጣት ስዩም አይነት ድጋፍ ለሚሹ በርካታ ህሙማን እፎይታን ፈጥሯል። አቶ መኮንን ጥላዬ በሆስፒታሉ "የነፃ ታካሚ በሽተኞች ማህበር" ተጠሪና ታካሚ ናቸው። የኩላሊት እጥበት ህክምና መውሰድ ከጀመሩ አምስት ዓመት ሞልቷቸዋል። ለሁለት ዓመታት በኮሪያ ሆስፒታል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት ህክምና ሲሰጥ

ለአንድ ጊዜ የኩላሊት እጥበት 3 ሺህ 500 ብር እያወጡ ሲታከሙ ቆይተዋል። በሳምንት ሶስት ጊዜ ህክምናውን መውሰድ የሚመከር ቢሆንም የኢኮኖሚ አቅማቸው እየተሟጠጠ ሲመጣ ከሶስት ወደ ሁለት፤ አንዳንዴ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ህክምናውን ይወስዱ እንደነበር ነግረውናል፡፡

በተለያዩ ተቋማት በስራ አስኪያጅነት ሲያገለግሉ እንደነበር የሚያነሱት አቶ መኮንን፣ ለህክምና የሚጠየቀው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ የነበራቸውን ጥሪት ጨርሰው በጓደኞቻቸውና በተለያዩ ወገኖች ድጋፍ ህክምናውን ሲያገኙ ቆይተዋል። የመጀመሪያውን ህክምና ከወሰዱ በኋላ ህመሙና ስቃዩ ሳይሆን ለሚቀጥለው የሚሆን ገንዘብ ከየት አገኛለሁ? የሚለው ከምንም በላይ ያሳስባቸው ነበር፡፡

በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የነፃ የኩላሊት እጥበት ህክምና ድጋፍ ማግኘቴ ከነበረብኝ ጭንቀት ገላግሎኛል፡፡ ልክ ተርቦ ቆይቶ እንጀራ ሲሰጠው እንደሚደሰት ሰው ተደስቻለሁ፡፡ ህክምናውም ደረጃውን በጠበቀ፣ ፅዱ፣ በተሟላ ማሽንና ደስ በሚል ከባቢ፣ የተጓዳኝ በሽታዎች ህክምና እየተሰጣቸው በጥሩ ሁኔታ እያገኙ እንደሆነ ነው የገለፁልን፡፡ በቅርቡ ለሶስት ዓመት የሚሆን ግብአት መገኘቱ ለህሙማን ትልቅ እፎይታን የፈጠረ መሆኑንም አክለዋል፡፡

ወጣት ስዩም በበኩሉ እንደገለጸው፣ የነፃ ህክምና በማግኘቱ በፊት ይኖርበት ከነበረው ዱከም አካባቢ ቀረብ ብሎ ቱሉ ዲምቱ ላይ ቤት ተከራይቶ መኖር እንዲችል አግዞታል፤ ትዳርም መስርቶ እየኖረ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ፣ ዶ/ር ተከተል እና የጤና ባለሙያዎች ታካሚዎችን በመንከባከብና የጎደለውን በማሟላት እያደረጉት ላለው ድጋፍም ምስጋና አቅርቧል፡፡

የኩላሊት ታማሚዎች ህክምና እንዲያገኙ ከሚሰሩ ማህበራት መካከል ተስፋ የኩላሊት ታካሚዎች ማህበር አንዱ ነው፡፡ ማህበሩ በኩላሊት ህሙማን አማካኝነት በ2010 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን 235 አባላት አሉት፡፡ በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት እያገኙ ከሚገኙ ታካሚዎች መካከል አንዱ እንደሆኑ የነገሩን የማህበሩ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍን አስረስ፣ በሆስፒታሉ ከሚሰጠው ህክምና በተጨማሪ፣ ሰሞኑን የተደረገው ድጋፍ ህክምናውን በስፋት ለመስጠት የሚያስችል፣ ተስፋ ሰጪና አስደሳች እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ታካሚዎቹ በኩላሊት ህመም የሚሰቃዩ፣ የህብረተሰቡን ድጋፍና እገዛ የሚፈልጉ በርካታ በመሆናቸው በሌሎች የከተማዋ ሆስፒታሎች አገልግሎቱን ማስፋት እንደሚያስፈልግና ባለሀብቶችም ድጋፋቸውን እንዲሰጡ የጠየቁት አቶ መስፍን፣ ከዚህ ባሻገር በቀጣይ የኩላሊት ንቅለ ተከላ የሚከናወንበት መንገድ ቢመቻች ጥሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

## ለሆስፒታሉ የተደረገው ድጋፍና ፋይዳው

ከሰሞኑ የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚሰጠውን የኩላሊት እጥበት ህክምና በተጠናከረ መልኩ ለመስጠት የሚያስችል 20 ማሽኖችና 10 ዘመናዊ አልጋዎችን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በተገኙበት ለሆስፒታሉ ድጋፍ አድርጓል። በተጨማሪም ለ180 ታካሚዎች ለሶስት ዓመት የሚሆን የኩላሊት እጥበት ግብአቶች ድጋፍ ከወንበሮች ጋር አድርጓል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፣ በኢኮኖሚ አቅም ማነስ ህክምና ባለማግኘት ህይወታቸው የሚያልፍ የኩላሊት ታማሚዎችን ህይወት ለመታደግ የከተማ አስተዳደሩ ከአምስት ዓመት በፊት ጀምሮ ለስራ ማስኬጃና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን ወጪ ሳያካትት በየዓመቱ 25 ሚሊዮን ብር በመመደብ በነፃ ህክምና እንዲያገኙ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የተደረገው ድጋፍም በሆስፒታሉ የሚሰጠውን የኩላሊት እጥበት ህክምና በእጥፍ የሚያሳድግና ለታካሚዎቻችን ትልቅ እፎይታ ይፈጥራል፡፡ ህይወት አድን ስራ በፈጣሪም፣ በሰውም ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ድጋፉን ያደረጉት የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ፣ ባለሀብቱ ሼህ መሀመድ አሊ አላሙዲን እንዲሁም በማዕከሉ ከታመሙት ጋር እየታመሙ በቅንነት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ባለሙያዎች ምስጋና ይገባቹኋል ብለዋል፡፡

የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው ህይወትን በመታደግ ስራ በመሳተፋቸው ደስተኞች መሆናቸውንና ወደፊትም የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል፡፡

በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት ማዕከል የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት ቡድን መሪ ሲስተር ህይወት ለገሰ እንደገለፁት፣ በአሁኑ ወቅት በማዕከሉ አጣዳፊ የኩላሊት መድከም እና ስር የሰደደ የኩላሊት ህመም እክል ላጋጠማቸው ሰዎች የህክምና አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የኩላሊት እጥበት ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ህክምና በመሆኑ ብዙዎች ታካሚዎች በራሳቸው ወጪውን ሸፍነው መታከም አይችሉም፡፡ በዚህም ምክንያት በየመንገዱ፣ በገበያ ቦታ፣ በየእምነት ተቋማት መታከሚያ ገንዘብ ለማግኘት እጃቸውን ሲዘረጉ ይታያል፡፡ በሆስፒታሉ ዕድሉን ያገኙ ታካሚዎች ከኪሳቸው ምንም ሳያወጡ በነጻ አገልግሎቱ እየተሰጣቸው ነው፡፡ በተጨማሪም መድሀኒትና ምርመራ በነፃ ያገኛሉ፡፡ የነጻ ኩላሊት እጥበት ህክምና በመሰጠቱ እፎይታ የሚያገኘው አንድ ታካሚ ብቻ አይደለም፡፡ ቤተሰብ፣ ጎረቤትና ማህበረሰቡ ጭምር እንጂ ይላሉ ሲስተር ህይወት፡፡

የዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር ተከተል ጥላሁን እንደገለፁት፣ ሆስፒታሉ በአዲስ አበባ ከተማ ትልቁ የኩላሊት እጥበት ህክምና የሚሰጥበት ተቋም ነው፡፡ እስከአሁን በሆስፒታሉ በቋሚነት ስር የሰደደ የኩላሊት ህመም ያለባቸው 86 እና 34 አጣዳፊ የኩላሊት መድከም የሚያጋጥማቸው ታማሚዎችን ጨምሮ በድምሩ 120 ታማሚዎች የኩላሊት እጥበት ህክምና እያገኙ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ የግብአት እጥረት ሲያጋጥም አገልግሎቱን ከማቆም ይልቅ በሳምንት ሁለት ጊዜ ሲሰጥ እንደነበር ያስታወሱት ዶ/ር ተከተል፣ ከሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የተደረገው ድጋፍ በግብአት እጥረት ምክንያት በተለያየ ጊዜያት ሲቆራረጥ የነበረውን አገልግሎት ያለምንም መቆራረጥ ለማስቀጠል ያስችላል፡፡ ድጋፉ አሁን ህክምና እያገኙ ያሉትን ጨምሮ 180 ታካሚዎች ለሶስት ዓመት ህክምና ለመስጠት የሚያስችል ሲሆን ተጨማሪ የግብአት ግዥ በመፈፀም በጥቅሉ እስከ 240 ለሚደርሱ ህሙማን ህክምናውን ለመስጠት እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

የኩላሊት እጥበት ህክምና ከመስጠት ባሻገር በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ህክምናውን ለመጀመር መታቀዱን ዶክተር ተከተል ጠቁመዋል፡፡ ማህበራዊ ኃላፊነት በመወጣት የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ትልቅ ምሳሌ ነው። ሌሎች ባለሀብቶችም ይህንን አርዓያነት በመከተል የህዝብ ጤናን በማስጠበቅ ከመንግስት ጎን እንዲቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

## ህክምናውን ለማስፋት ምን እየተሰራ ነው?

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ እንደ ከተማ አስተዳደር የኩላሊት እጥበት ህክምና በዘውዲቱ መታሰቢያ እና በዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡

አገልግሎቱን በሌሎች ሆስፒታሎች ከማስፋት አኳያም፣ በዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የመዲናዋ ኪነ-ጥበባዊ ዝግጅቶች




ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ ከተሰናዱ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

በአብርሃም ገብሬ

በመዲናችን አዲስ አበባ ባለፉት ቀናት የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የቴአትር ምርቃት፣ የመጽሐፍት ውይይቶችና የሥዕል አውደ-ርዕይ ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

ዛሬ ቅዳሜ ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጀምሮ የገጣሚ አንዱ ጌታቸው የግጥም መድብል በሆነው "ስካርፍ፣ ቡና እና ጢስ" በተሰኘው የግጥም መድብል ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ አራት ኪሎ ኢክላስ ሕንጻ ውስጥ በሚገኘው በዋልያ መጽሐፍት አዳራሽ የሚደረገው ይሄ ውይይት፣ የጥበብ አፍቃሪያን ተገኝተው የውይይቱ አካል እንዲሆኑ ተጋብዘዋል።

በሌላ መረጃ፣ "የወዲያ ነሽ" ልብወለድ መጽሐፍ እንደገና ለንባብ ሊበቃ ነው፡፡ በአንጋፋው ደራሲ ሃይለመለኮት መዋዕል የተደረሰው ይህ መጽሐፍ ለዓመታት ከገበያ ጠፍቶ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ላይ እንደገና ለአንባብያን እንዲደርስ እየተሰራ መሆኑ ደራሲው አሳውቋል፡፡

የደራሲው የመጀመሪያ ድርሰት የሆነው ይኸው ልብወለድ መጽሐፍ፣ በቅድመ-ሽያጭ ዘዴ በማህበራዊ ሚዲያ በኩል ለገበያ ቀርቧል፡፡ የመጽሐፉ ዋጋ 400 ብር ሲሆን፣ አንባብያን በደራሲው በኩል መጽሐፉን እንዲገዙና ያሉበት ቦታ ድረስ እንደሚልክላቸው በማህበራዊ የትስስር ገጹ አሳውቋል፡፡

## ሥዕል

"የቀለማት ግለ-ዝና" የተሰኘና የሰዓሊ እያሱ ተላይነህ የሥዕል ሥራዎች የቀረቡበት አውደ-ርዕይ ሐምሌ 2 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በሀያት ሪጀንሲ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል በመታየት ላይ ነው፡፡ አውደ-ርዕዩ እስከ ፊታችን ሐምሌ 28 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ለጥበብ አፍቃሪያን ክፍት ሆኖ ይቆያል።

## ሲኒማ

በታዋቂዋ የፊልምና የቴአትር ባለሙያ መዓዛ ወርቁ የተጻፈውና የተዘጋጀው "እመጌቶች" ቴአትር ነገ እሁድ ሐምሌ 13 ቀን 2017 ዓ.ም ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ይመረቃል፡፡ ቴአትሩ የሚመረቀው በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን የጥበብ ወዳጆች ምርቃቱ ላይ ተገኝተው እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል።

## ሌሎች መሰናዶዎች

በኒውሮሳይንስና ጥበብ ላይ ያተኮረ ልዩ ዝግጅት የፊታችን ሰኞ ሐምሌ 14 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 ሰዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ሊደረግ ነው፡፡ በዚህ ልዩ መርሐ-ግብር ላይ "ሲናፕስ ኢትዮጵያ" በይፋ ሊጀመር እንደሆነ አዘጋጆቹ ለመገናኛ ብዙሃን አስታውቀዋል። "ሲናፕስ በኒውሮሳይንስ አለም እጅግ መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። ሁለት ነርቭ ሴሎች ተገናኝተው መረጃ የሚለዋወጡበት ድልድይ ማለት ነው። ይህንን መነሻ በማድረግ፣ ሲናፕስ ኢትዮጵያ በሀገራችን የመጀመሪያው በኒውሮሳይንስ ላይ ያተኮረ የህዝብ ንግግርና ውይይት መርሃ ግብር ነው። በመርሃ ግብሩም ስለ ኒውሮሳይንስ የቅርብ ጊዜ ዕውቀቶችና ምርምሮች በመድረኩ ይቀርባሉ" በማለት አዘጋጆቹ ለመገናኛ ብዙሃን አሳውቀዋል፡፡

አዘጋጆቹ የኒውሮሳይንስ ዕውቀት በጤና፣ በትምህርት እና በሌሎችም የህይወታችን ዘርፎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም "በተመራማሪዎችና በዝግጅቱ ታዳሚዎች መካከል የልምድ ልውውጥና አዲስ ግንኙነት ይፈጠራል። ጎን ለጎን ስነ-ጥበባዊ ዝግጅቶችም ይቀርባሉ። የሳይንስና የኪነ-ጥበብ ውህደት በፈጠረው ልዩ ድባብ እንዝናናለን" ሲሉም አስታውቀዋል።

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ ከሚታዩ ቴአትሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ ቅዳሜ 8:30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ እና 11:30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች፤ እሁድ በ8:00 ሰዓት 12ቱ እንግዶች፣ 11:30 ሰዓት እምዬ ብረቷ በብሔራዊ ቴአትር ይታያሉ፡፡ በቀጣይ ቀናት ይኼው ቀጥሎ ማክሰኞ በ11:30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11:30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ 11:30 ሰዓት ሽምጋይ፣ አርብ በ11:30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በዚሁ ቴአትር ቤት ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ መልሱን ለማግኘት ግራና ቀኝ ላይ ያሉ ቁጥሮች እንደምራለን፡፡ ደምረን ያገኘነው ቁጥር በስንት ብናካፍለው ነው የመሃሉ ቁጥር ሊመጣ የሚችለው? የሚለውን በመጀመሪያ መመለስ አለብን፡፡ ለማካፈል የምንጠቀመው ቁጥር ለሶስቱም ተመሳሳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመጀመሪያ ላይ የተቀመጠው ጥያቄ መልስ እንዴት እንደተሰራ አብረን እንየው፡፡ 19 + 17 = 36 ይሆናል፡፡ የመሃሉ 9 ለማግኘት 36ን ለ4 እናካፍለዋለን፤ 36÷4= 9 ይሆናል፡፡ 4 ቁጥር የጋራ አካፋይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የጥያቄው ትክክለኛ መልስ 11 ይሆናል። አሰራሩ ደግሞ 13 + 31 = 44 ከዚያ ደግሞ 44 ÷ 4 = 11 ይሆናል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ክረምትና ኪነ ጥበብ

በጊዜው አማረ

ክረምት በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ነገር ነው፡፡ የዝናብ ወቅት በመሆኑ በተለምዶ ከግብርና ሥራ ጋር በብዛት ይያያዛል። ሆኖም ከዚህ በተሻገረ መንገድ ለብዙኃኑ ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች፣ ገጣሚያን፣ ሙዚቀኞች እና የዕደ-ጥበብ ባለሙያዎችም ጥልቅ የመነሳሳት ምንጭ ነው ማለት እንችላለን።

በተጨማሪም ክረምት ለአዲሱ ዓመት የመድረስ ተስፋ ጎልቶ የሚታይበት ነው። የዝናብ፣ የመብረቅ፣ የውሃ ሙላትና ጎርፍ ወቅት ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታ የእርሻ ወቅት ነው፡፡ ለተማሪዎች የእረፍት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኪነ ጥበብ ልምድ መለዋወጫ፣ የንባብ ጊዜም ነው። በርካቶች በተለይ በ1990ዎቹ በክረምት ወቅት መጽሐፍ እየተዋዋሱ ማንበብ ሁልጊዜም የሚያስታውሱት ትዝታቸው ነው፡፡

ተሻለ ከበደ በተግባረድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የአርክቴክቸር መምህር ናቸው። ረጅም ዓመት የንባብ ልምድ ያላቸው ሲሆን የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ሂሶችንም በመጻፍ ይታወቃሉ፡፡ እርሳቸው ከዚህ ቀደም በጉዳዩ ላይ ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት ሃሳብ “በቀደሙት ጊዜያት በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ያሉ ወጣቶችና ጎልማሶች ክረምትን ከንባብና ኪነ ጥበብ ጋር በማስተሳሰር ረገድ ተቀራራቢ ትዝታ ያለን ይመስለኛል። ምክንያቱም በጋው ወራት አብዛኛው ጊዜያችንን የምናሳልፈው ትምህርት ቤት ውስጥ በመሆኑ፣ ሰኔ ሰላሳ ትምህርት ከተዘጋ በኋላ ትምህርት ቤት ውስጥ እናሳልፈው የነበረውን ሰዓት በሌላ ነገር ላይ ማዋል የግድ ይላል። እኔም ክረምቱን በማንበብና ፊልም በማየት ነበር የማሳልፈው፡፡ በዚያን ጊዜ በተለይ በየቀኑ ይታተሙ የነበሩ በተለይ የስፖርት፣ የፍቅርና የኪነ ጥበባዊ ጋዜጣዎችንና መጽሔቶችን ተከራይቼ አነብ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም አካባቢያችን ውስጥ የመጽሐፍት ኪራይ ስለነበር ብዙ የልብ ወለድ ድርሰቶችን ያነበብኩት በዚሁ የክረምት ወራት ነበር፡፡ ስለዚህ ክረምትና ንባብ የትዝታዎቼ አካል ናቸው” ሲሉ አጫውተውናል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ የኪነ ጥበብ ቡድን መሪና ሙዚቀኛ ዘላለም እሸቱ ደግሞ ክረምት በሀገራችን ከኪነ ጥበብ ጋር ያለው ቁርኝት እጅግ ከፍተኛ ነው ይላል። ምክንያቱም ክረምት ራሱ በኪነ ጥበብ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በርካታ የኪነ ጥበብ መርሃ ግብሮችና ትምህርቶች ይከናወኑበታል፡፡

ለምሳሌ እኛ በዚህ ክረምት የችግኝ ተከላ ማነቃቂያን የበጎ አድራጎት ኪነ ጥበባዊ ስራዎችን ለማከናወን በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ ከሰሞኑም ከአንጋፋ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ እያደረግን ነው በማለትም ያክላል፡፡

ክረምት በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ስራዎች ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው ወቅት ነው። በግጥም ስራዎች ላይ ዳመናው፣ ዝናቡ፣ ናፍቆቱ ተገልጿል፡፡ በፊልም ስራዎች ላይም ዝናብ አንድ የፊልሙ ግብዓት ወይም መቼት ሆኖ እናገኘዋለን። በሙዚቃ ደግሞ ዋነኛ ጭብጥ ሆኖ ይስተዋላል፡፡ ድምጻዊ መስፍን በቀለ፡-

“በክረምት ወር ሐምሌ ነሀሴ

ከኔ ሌላ አለ ትራሴ

እንደሌለኝ የሚያሞቅ ሰው

የሚነግርሽ ኧረ ማነው.

እሱስ ይሁን ይነገርሽ

ለኔ ካዘነ ልብሽ

መጥተሽ ላትገቢ ከእቅፌ

ለምን ይጥፋ እንቅልፌ....

ነይ በክረምት ነይ በብርዱ

ሰው አይችልም ሆዱ...” እያለ የዘፈነውም ለዚሁ ይመስላል፡፡

ክረምት የኢትዮጵያ ገጽታ በአረንጓዴ ምንጣፍ የሚሸፈንበት ወቅትም ነው። የወንዞችና ፏፏቴዎች መሙላት፣ የተራራማ አካባቢዎች ጭጋጋማ ውበት፣ እንዲሁም የሰማይ ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸው ደመናዎች፣ የመብረቅ ብልጭታና ቀለማት ለበርካታ ሰዓሊያንና ፎቶ ግራፍ አንሺዎች እንዲሁም የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የሃሳብ ምንጭ ናቸው፡፡ ለገጣሚያን ማራኪ ስንኞች ገጸ በረከት ናቸው፡፡ የዝናብ ጠብታዎች፣ የአፈር ሽታ እና ከዝናብ በኋላ የሚፈጠረው አዲስ ሕይወት ስሜትን የሚቀሰቅስ ከመሆኑም በላይ ለፈጠራ ሥራዎች መነሻ ሆኗል፡፡

በክረምት ወቅት የሚታየው የተፈጥሮ ለውጥ አስገራሚ ነው። በዝናብ የሚሸፈነው መስክ፣ የወንዞች ሙላት፣ ጎርፉ፣ የሰዎች አለባበስ፣ የዛፎቹ ውዝዋዜ፣ የጭጋጉ መንፈስ... እነዚህ ሁሉ ሕይወት የሚዘሩ እና ስሜትን የሚይዙ የእለት ተእለት ትዕይንቶች ናቸው፡፡ ዝናብ በሚጥልበት ወቅትም በሰዎች ላይ የሚፈጠረው ስሜት የተለየ ነው ይላሉ፤ ባለሙያዎች፡፡

አይሻውርያ ሙሩዲ የተባሉ ምሁር “Raindrops and Ink Blots: How Rain Inspires Creativity” በሚል ርእስ ባስነበቡት ጽሑፍ ላይ እንዳብራሩት፣ ክረምት በተለይ ዝናብ ሲሆን አርቲስቶችን፣ ደራሲያንን እና ሙዚቀኞችን ለአዲስ ፈጠራ ያነሳሳል፡፡ ከቀላል ዝናብ እስከ አውሎ ነፋስ የቀላቀለ ውሽንፍር እና ነጎድጓድ ድረስ ስፍር ቁጥር በሌላቸው የጥበብ ሥራዎች ውስጥ ተንጸባርቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍም የክረምት ወራት በተለይም ለቅኔና ግጥም ወሳኝ ቦታ አላቸው። ገጣሚያን የዝናቡን ወቅት ከኃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ፍልስፍናዊ ትርጉሞች ጋር በማያያዝ በርካታ ሥራዎችን አበርክተዋል። የግብርናው ሥራ፣ የገበሬው ድካም፣ እንዲሁም የዝናብ በረከት፣ በብዙ ግጥሞችና ታሪኮች ውስጥ ተንጸባርቀዋል።

ሰኔ ደግሞ መጣ ክረምት አስከትሎ

ገበሬው ተነሣ ማረሻውን ስሎ፡፡

ሐምሌም ተከተለ ገባ ዝናብ ጭኖ

ቀንና ሌሊቱን በዝናብ ጨፍኖ፡

ነሐሴ ተተካ ኃይለኛው ክረምት



ፎቶ- ከገፀ ድር

የክረምትና ኪነ ጥበብን ትስስር ከሚያሳዩ የሀገራችን ጥበባዊ ስራዎች መካከል አንዱ

ያወርደው ጀመረ የዝናብ መዓት፡፡...

የሚለው የከበደ ሚካኤል ታዋቂ ግጥምን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ባደረግነው አጭር ዳሰሳ ስለክረምት የተሰሩ በርካታ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች የሚያንጸባርቁት ፍቅርን፣ ተስፋን፣ ናፍቆትን እና ብቸኝነትን ነው፡፡ ታዋቂው ገጣሚ ጌትነት እንየው፡-

ባዶ ቤት በክረምት

አንች የሌለሽበት

ዝም ጸጥ ብቻ

ጣሪያ መጫወቻ፡፡

... አመሻሽ

ኦና ቤት

አንች የሌለሽበት

ፀጥ-ረጭ፣ ብቻ

ወለል መጫወቻ... ሲል የተቀኘው ስራ ሁነኛ አስረጅ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በተጨማሪም ገጣሚ ዮናስ እሸቱ ክረምትን የተመለከተ ተወዳጅ እና ታዋቂ ግጥም አለው፡፡ ይህ ግጥምም፤ ናፍቆትን፣ ተስፋንና መጠበቅን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

ዘመን ዘመንን ሲወልድ ጊዜን እየተካ

በጋው ተገባዶ ክረምት ሲያሽካካ

በኮከብ ታጅባ ጨረቃ ስትፈካ

ከውቢቷ ሰማይ ፅልማሞቱን ገልጣ ፀሀይ ስትወጣ

ይህ ሁሉ ሲነጉድ ቀናት እየሄደ ቀናት እየመጣ

እኔ ግን እዛው ነኝ ትመጫለሽ እያልኩ ከሀሳብ ሳልወጣ፡፡

በውቀቱ ስዩምም እንዲሁም የክረምትን መልክ ከገለጹ ገጣሚያን መካከል አንዱ ነው፡፡ ልረሳሽ እየጣርኩ ነው በተሰኘው ስራው፡-

...መጣ፣ መጣ ፣መጣ፣ የዝናቡ ኮቴ አየለ

ክረምት የፍጥረት መሲሕ፣ በቀጠሮው ከተፍ አለ፡፡

ስስ የጉም አይነርግብ፣ ውብ ገጽሽን ሸፋፈነው

የርጥብ አፈር፣ ርጥብ ሽታ፣ ውብ ሽቶሽን አዳፈነው

ልረሣሽ እየጣርኩ ነው፡፡

የዝናቡ ኮቴ ይደምቃል

እንደ ብስል ሾላ ፍሬ፣ አሮጌው ሰማይ ይወድቃል

አዲስ ሰማይ ይነቃል

አዲስ ጅረት ይፈልቃል... ሲል ተቀኝቷል፡፡

በሀገራችን የክረምት ወቅት ከባድ የግብርና ሥራ የሚበዛበት ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ የዝናቡ ብዛት ሰዎችን በቤት ውስጥ እንዲቆዩ ያስገድዳል። ይህ ደግሞ ለቤተሰብ መሰባሰብ፣ ታሪክ ለመተረክ፣ ግጥም ለማንበብ ወይም የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለመለማመድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በርካታ የእደ-ጥበብ ባለሙያዎችም በዝናብ ወራት የሽክላ ሥራ፣ የሽመና እና ሌሎች የቤት ውስጥ ጥበቦችን በመሥራት ጊዜያቸውን ይጠቀማሉ። በመዲናችን አዲስ አበባ ደግሞ ጀማሪ ከያንያን ኪነ ጥበብን ከእኩዮቻቸው ወይም ከአንጋፋዎቹ የሚማሩበት እንዲሁም የሚያነቡበት ጊዜ ነው፡፡

የኪነ ጥበብ ባለሙያው ዘላለም እሸቱ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ክረምትና ኪነ ጥበብን በተመለከተ በሰጠው ሃሳብ ጥላሁን ገሰሰን ጨምሮ በርካቶች ስለክረምት ዘፍነዋል፡፡ ክረምት በኪነ ጥበብ ከመገለጹ በዘለለ ኪነ ጥበብን መማሪያ ወቅትም ነው፡፡ እኛ ከአንጋፋዎች እንማራለን፡፡ የተማርነውን ደግሞ በዘንድሮው ክረምትም ልምድና እውቀታችንን ለተማሪዎችና ለጀማሪ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ለማካፈል ዝግጁ ነን ይላል፡፡ ዘላለም እሸቱ፡፡

የሃበሻ ኳየር መስራችና የኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢተው ዳዊት ከሰሞኑ በጎ አድራጎት፣ ክረምትና ኪነ ጥበብን በተመለከተ የሰጠው አስተያየትም ከዘላለም ሃሳብ ጋር የሚስማማ ነው፡፡

ቢተው ኪነ ጥበብ ሌሎችን የማስተማር፣ የማነቃቃትና የማስተባበር አቅም ጥልቅ፣ በልኩ ያልተነገረለት እና ያልተሰራበት ነው፡፡ ኪነ ጥበብ ትልቅ ሃይል ነው፡፡ ይህን ሃይል ደግሞ ለበጎ አድራጎት ስራዎች፣ ለአረንጓዴ ልማት፣ ለመተጋገዝና ቀና ለሆኑ ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ክረምትም አረንጓዴ አሻራ፣ በጎ አድራጎትና ሌሎችን ስራዎች በኪነ ጥበብ የማነቃቃትና የመግለጽ ሃሳቡ አለን ሲልም አብራርቷል፡፡

# ልጆች፤ የንባብ ልምዳችሁ እንዴት ነው?



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በክረምት ወቅት ህፃናት ንባብን ከሚያዳብሩበት አንዱ የአብርሆት ቤተ መጽሐፍት ነው

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ወቅቱ ክረምት እንደመሆኑ ትምህርት ቤት ተዘግቶ እረፍት ላይ ናችሁ፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ ቤተ-ዘመድ በመጠየቅ፣ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመጫወት፣ የልጆች ፊልም በማየት፣ ስዕል በመሳል ወይም የተለያዩ መጽሐፍትን በማንበብ ታሳልፉላችሁ ብለን እናስባለን፡፡ አዎ! ልጆች ትኩረታችሁን ይበልጥ ማንበብ ላይ ካደረጋችሁ የሁልጊዜ እውቀትን ታገኛላችሁ፡፡

ስለዚህ ልጆች በዛሬው ፅሁፋችን ለእናንተ ልናሳውቃችሁ የወደድነው መጽሐፍ ማንበብ የሚያስገኘውን ጥቅም ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የእረፍት ጊዜያቸውን መጽሐፍት በማንበብ የሚያሳልፉ ልጆችን ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡

"ስሜ ቅዱስ አዲሱ ይባላል፡፡ የምኖረው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ነው፡፡ በልደታ ካቶሊክ ካቴድራል የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡

ትምህርቴን በአግባቡ እከታተላለሁ፤ ለፈተና ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም አነብባለሁ፡፡ አሁን ደግሞ እረፍት ስለሆንኩ ለማንበብ ይመቸኛል፡፡ የመማሪያ መጽሐፍትን በብዛት፣ የተረትና የልብወለድ መጽሐፍትን ደግሞ አልፎ አልፎ አነብባለሁ፡፡ የማነበው ግን ከጠዋት እስከ ማታ አይደለም፤ መጫወት ባለብኝ ሰዓት እጫወታለሁ፤ ፊልም አያለሁ፤ ቤተሰቦቼንም በስራ አግዛለሁ፡፡

መጽሐፍትን በማንበቤ ጥቅም አግኝቼበታለሁ፤ በዚህም በፊት 12ኛ ደረጃ የምወጣውን አሁን 5ኛ ደረጃ እንድወጣ አድርጎኛል፡፡ ለዚህም ደግሞ ከጎኔ ሆነው የሚያግዙኝ ቤተሰቦቼ ናቸው" ብሏል፡፡

በእረፍት ላይ ያላችሁ የትምህርት ቤት እና የሰፈር ጓደኞቼ ክረምትን የማሳልፈው በመጫወት እና በማንበብ ነው፡፡ እናንተስ? ብላ የጠየቀቻችሁ ደግሞ ሊዲያ ህሉፍ ናት፡፡ "የምማረው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ይሐ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አካዳሚ ትምህርት ቤት ነው። በቀጣይ ዓመት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ክረምት ሲመጣ ከሚያስደስቱኝ ነገሮች ውስጥ መጽሐፍት ማንበብ አንዱ ነው። በተለየ ሁኔታ ለትምህርቴ የሚረዱኝን መጽሐፍት አነባለሁ፡፡ በዚህ ክረምት የማነባቸው አስራ አንድ የ7ኛ ክፍል መጽሐፍት ተገዝተውልኛል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ትኩረቴን ጨዋታ ላይ ካደረግኩ እንኳን ማንበብ እንዳለብኝ ከቤተሰቦቼ ይነገረኛል፡፡ ዘንድሮ 4ኛ ደረጃ ነው የወጣሁት፡፡ ለወደፊት ከ1ኛ እስከ 2ኛ ደረጃ ለመውጣት አነብባለሁ፡፡ ስለዚህ ጓደኞቼ እረፍታችሁን በጨዋታና ፊልም በማየት ብቻ ከምታሳልፉ ማንበብንም ልምዳችሁ አድርጉ"፡፡ ብላለች፡፡

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሳለሚያ አካባቢ የቤተልሔም ዩዝ አካዳሚ የ6ኛ ክፍል ተማሪዋ መከሊት መንግስቱ፣ "የ6ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ተፈትኜ ወደ 7ኛ ክፍል አልፌያለሁ፡፡ ትምህርት እወዳለሁ። በክረምቱ የእረፍት ጊዜዬ መጽሐፍ ማንበብ ያስደስተኛል፡፡ ትኩረቴን የማደርገው ደግሞ ለትምህርቴ አጋዥ በሆኑ እና በተረት መጽሐፍት ላይ ነው፡፡ አልፎ አልፎም አጫጭር ልብወለዶችን ማንበብ እወዳለሁ፤ ተረቶችን ደግሞ ከስልኬ ላይ አነብባለሁ፤ ቤተሰቦቼም መጽሐፍት ይገዙልኛል፤ እንዳነብም ይመክሩኛል፤ ያበረታቱኛል፡፡

መጽሐፍትን ሳነብ ደስታ ይሰማኛል፡፡ በማንበቤ ምክንያትም የማላውቃቸውን ነገሮች እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ የንባብ ፍጥነቴም ጨምሯል፡፡ ከዚህ በላይ ለማወቅና በትምህርቴም ውጤታማ ለመሆን ማንበብ እንዳለብኝ አምናለሁ። ሌሎች ጓደኞቼም እንደ እኔ ቢያነቡ እላለሁ፡፡" ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች፡፡

ልጆች የክረምት ጊዜያቸውን በንባብ የሚያሳልፉ ጓደኞቻችሁን የንባብ ልምድ አነበባችሁ አይደል? ጎበዞች! ማንኛውም ሰው ካነበበ ሁሉንም ነገር መስራት የሚችልና ጎበዝ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ አንብቡ እያልን፣ መልካም ክረምት! መልካም የዕረፍትና ንባብ ጊዜ ተመኘንላችሁ!

# 5 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ብዙ ቁልፎች ያሉት ነገር ግን አንድ መቆለፊያ የማይከፍተው ምንድን ነው?**

**መልሱ፡- ሀ. ፒያኖ**

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ወተቱ ጥቁር ማለቢያው ነጭ ምንድ ነው?**

ሀ. ጀበና
ለ. ቡና
ሐ. ሻይ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# “የመዲናዋን ገፅታ በማሻሻል በኩል ተጨባጭ ለውጥ አምጥተናል”

**የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር ሙህዲን ረሻድ**

- **በ2017 በጀት ዓመት 371 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የመንገድ መሰረተ ልማት መገንባት ተችሏል**



ፎቶ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን
ቃሊቲ ቅሊንጦ መንገድ

ፎቶ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን
ከአፍሪካ ህንፃ -ጀሞ መስታወት ፋብሪካ መንገድ

**በላዋይሽ ቢተው**

መንገድ አይኑ ይፍሰስ አይባልም ደርሶ፣

የወሰደውን ሠው ያመጣል መልሶ… የሚለው ስነ-ቃል የመንገድን አስፈላጊነት የሚያመላክት ነው፡፡ መንገድ አድራሽ ነው፤ መንገድ አሻጋሪ ነው፤ መንገድ አገናኝ ነው፡፡ የተራራቀን ከማገናኘት ባለፈ ለግለሰቦች እና ለሀገር እድገትም የጀርባ አጥንት ነው፡፡ የመንገድ መስፋፋት የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ትልቅ መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡ ከ50 በመቶ በላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ለሚንቀሳቀስባት አዲስ አበባ ሲሆን ደግሞ ዋጋው ከዚህም በላይ ከፍ ያለ ነው፡፡

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የከተማዋን የመንገድ ተደራሽነት ከፍ ለማድረግ የግንባታና ጥገና ስራዎችን በከፍተኛ ትጋት 24/7 (ሰባቱንም ቀናት ሃያ አራት ሰዓት) እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ሽፋኑን ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በርካታ መንገዶችን ገንብቶ ለአገልግሎት እንዲውሉ አድርጓል፡፡ ሰኔ 29 ቀን 2017 ዓ.ም የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ጠቅላላ ርዝመታቸው 31 ነጥብ 5 ኪ.ሜ. የሆኑ 21 የመንገድ ፕሮጀክቶች በአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተመርቀዋል፡፡

በምረቃ ስነ ስርዓቱ ወቅት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባደረጉት ንግግር፣ “የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን፣ የመንግስት እና የግል ኮንትራክተሮች፣ አማካሪ ድርጅቶች፣ የክፍለ ከተማ አመራሮች እንዲሁም ነዋሪዎች ፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ተጠናቅቆ ለአገልግሎት እንዲበቁ ላበረከታችሁት አስተዋጽኦ በራሴ እና በከተማ አስተዳደሩ ስም ምስጋና አቀርባለሁ” ብለዋል፡፡

“ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ባከናወናቸው መጠነ ሰፊ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ የነዋሪዎችን ጥያቄ መልሰናል፤ የመዲናዋን ገፅታ በማሻሻል በኩል ተጨባጭ ለውጥ አምጥተናል” ያሉት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር ሙህዲን ረሻድ ናቸው፡፡

“ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመጣው የመንገድ ግንባታ አፈፃፀማችን የተገኙ ጠቃሚ ልምዶችን እንደ ግብዓት በመውሰድ እና የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን መነሻ በማድረግ፣ አዲስ አበባ ያላትን ድርብርብ የመዲናነት ሚና የሚመጥን ዘመናዊ የመንገድ መሠረተ-ልማት ተደራሽ ለማድረግ፤ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ በትጋት እየሠራን እንገኛለን” ሲሉም አክለዋል፡፡

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የከተማዋን የመንገድ ኔትዎርክ ደህንነቱ ተጠብቆ የተቀላጠፈ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር በ2017 በጀት ዓመት የአስፓልት፣ የኮብልስቶን ንጣፍ፣ የጠጠር እና የእግረኛ መንገድ፣ የድጋፍ ግንብ እና ድሬኔጅን ጨምሮ 371 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የመንገድ መሰረተ ልማት መገንባት መቻሉንም ነው የገለፁት፡፡

እንደ ኢንጂኒዬር ሙህዲን ገለፃ፣ በበጀት አመቱ 1021 ኪሎ ሜትር የተለያዩ የጥገና ስራዎችን በማከናወን የትራፊክ ፍሰቱን እና የመንገድ ደህንነቱን ማስጠበቅ ተችሏል፡፡

ባለስልጣኑ ከሌሎች ኮንትራክተሮች ጋር በቅንጅት ከሰራቸው ፕሮጀክቶች መካከል ቀዳሚዎቹ የቃሊቲ - ቅሊንጦ እና የቃሊቲ - ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ የቃሊቲ ቅሊንጦ የመንገድ ፕሮጀክት 10 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 50 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ሲሆን ተጨማሪ 5 ድልድዮችን አካትቶ የተገነባ ነው፡፡ በተመሳሳይ የቃሊቲ አደባባይ -ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 11 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 50 ሜትር ስፋት ከተጨማሪ ሶስት ተሸጋጋሪ ድልድዮች ጋር ተገንብቶ ለምረቃ በቅቷል፡፡ ሁለቱም ፕሮጀክቶች የማህበረሰቡን የመንገድ አገልግሎት ችግር ከመቅረፍ አንፃር ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በቦታው ላይ የሚስተዋለውን የትራፊክ እንቅስቃሴ መጨናነቅ በእጅጉ ይቀንሳሉ፡፡

በሌላ በኩል ባለስልጣኑ በራሱ አቅም አጠናቅቆ ለትራፊክ እንቅስቃሴ ክፍት ካደረጋቸው ፕሮጀክቶች መካከል፣ ከአፍሪካ ህንጻ - ጀሞ መስታወት ፋብሪካ፣ ከቂርቆስ ማርገጃ - ቡልጋሪያ፣ ከቤላ መንገድ - ፈረንሳይ ፓርክ - አቦ ቤተ ክርስቲያን እና ናሳው ሪል ስቴት - አርሴማ ቀለበት መንገድ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ለምረቃ የበቁት የመንገድ መሰረተ ልማቶች የከተማዋን የመንገድ ሽፋን ከማሳደጋቸውም ባሻገር የአዲስ አበባን ገፅታ በማሻሻል በኩል ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በቀጣይም በከተማዋ በሁሉም አቅጣጫ እያካሄደ የሚገኘውን የመንገድ መሰረተ-ልማት የማስፋፋት እና ተደራሽ የማድረግ ተልዕኮውን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ኢኮኖሚ

# ማህበራቱ የገበያውን ሚዛን ምን ያህል እያስጠበቁ ነው?

- **የ90 ቀናት ዕቅዱ ኮሚሽኑ ለጀመረው የሪፎርም ትግበራ ትልቅ አቅም እንደሆነለት ተገልጿል**

**በደረጀ ታደሰ**

አቶ ታደሰ ጎሳዬን እና ባለቤቱን ወይዘሮ ፍሬሕይወት ለገሰን ያገኘናቸው ለመሰረታዊ ፍጆታ የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት ሲገዙ ነው፡፡ ከገዟቸው ምርቶች መካከል፡- ዕንቁላል፣ ፓስታ እና ዘይት ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ግብዓቶች ለመግዛት የመረጡት ደግሞ የመሰረታዊ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ሱቅን ነው፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት መሠረታዊ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበር ሱቅ የተገኙት አቶ ታደሰ እና ባለቤታቸው፤ የመሰረታዊ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ሱቅ አገልግሎትን በአብዛኛው እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ፡፡ ለዚህም በማህበራቱ የሚቀርቡ ምርቶች በሌሎች ነጋዴዎች ከሚቀርቡት አንፃር በዋጋም ሆነ በጥራት የተሻሉ መሆኑን በዋና ምክንያትነት ያነሳሉ፡፡

በዕለቱ ግዢ የፈፀሙትን የምርት ዓይነትና ዋጋቸውን በነጋዴው እየተሸጡ ካለበት ወቅታዊ ዋጋ ጋር በማነፃፀር ሃሳባቸውን ያጋሩን ወይዘሮ ፍሬሕይወት እንደገለፁት፤ በሸማች ህብረት ሥራ ማህበር የቀረቡ ምርቶች በአካቢያቸው ካሉት ሱቆች አንፃር ቀላል የማይባል የዋጋ ልዩነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ከማህበሩ ሱቅ በ15 ብር ሂሳብ የገዙት ዕንቁላል በነጋዴዎች ሱቅ ከ22 ብር በላይ ነው። ፓስታ በ90 ብር ሂሳብ የገዙ ሲሆን፤ በሱቆች ከ10 ብር ያላነሰ ጭማሪ አለው፡፡ በተመሳሳይ በ1 ሺህ 480 ብር የገዙት ባለ 5 ሊትር ዘይት በነጋዴ ሱቆች ከ1 ሺህ 600 ብር በላይ በሆነ ዋጋ ነው የሚሸጠው፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች ከነዋሪው ፍላጎት ጋር አቅማቸው እንዲያድግ ማድረግ ያስፈልጋል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለህብረተሰቡ መሰረታዊ ግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን የሚያቀርቡ 11 ዩኒየኖች እና 154 መሠረታዊ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት የሚገኘው መሠረታዊ ሸማች ማህበር አንዱ ነው፡፡ ይህ ማህበር እንደ ሌሎቹ ሁሉ፤ የኑሮ ውድነትን ለማቃለል የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል። ማህበሩ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የፍጆታ ምርቶችን ያቀርባል፡፡ በተጠናቀቀው የ2017 በጀት ዓመትም ከፍተኛ መጠን ያላቸው ምርቶችን በመጠን፣ በጥራት፣ በዋጋ ከነጋዴው በተሻለ ሁኔታ በማቅረብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

አቶ ይታየው ታደለ፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ አራት መሰረታዊ ሸማች ማህበር ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚገልፁት በወረዳው ከሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል ውስጥ 3 ሺህ 645 የሚሆኑት የማህበሩ አባላት ናቸው፡፡ ለእነዚህ አባላት እና ለሸማቹ ሕብረተሰብ ምርቶቹን በተሻለ ጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ ይገኛል፡፡ ይህንን መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት (ሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም.) ማህበሩ ሰርገኛ ጤፍ 11 ሺህ 600 ብር በኩንታል፣ ቀይ ጤፍ 10 ሺህ 200 ብር በኩንታል፣ ዱቄት 91 ብር በኪሎ ግራም፣ ፓስታ 90 ብር፣ 5 ሊትር ዘይት 1 ሺህ 480 ብር እየተሸጠ ይገኛል፡፡

በገበያ ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እያሳየ ያለው የዕንቁላል ምርት በመሰረታዊ ማህበሩ በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረበ እንደሚገኝ አቶ ይታየው አስረድተዋል። እንደሳቸው ገለፃ፤ አንድ ዕንቁላል በ15 ብር እየተሸጠ ይገኛል፡፡ በአንድ ሳምንት ውስጥ ከ5 ሺህ በላይ ዕንቁላል ለተጠቃሚዎች ቀርቧል፡፡ አንድ ዕንቁላል በነጋዴ ሱቆች እስከ 23 ብር እየተሸጠ ሲሆን፤ በማህበሩ የሚቀርበው ከዚህ አንፃር በዋጋ ደረጃ ከፍተኛ ቅናሽ አለው። በማህበሩ የሚቀርበው ዕንቁላል ዋጋ ቅናሽን ምክንያት በማድረግ ብዛት ያለው እንቁላል የመግዛትና ላልተፈለገ ዓላማ (ለነጋዴዎች አትርፎ የመሸጥ) ፍላጎት ስላለ፤ አንድ ሸማች እስከ 30 ዕንቁላል ብቻ እንዲገዛ ይደረጋል፡፡

አክለው እንዳብራሩት፤ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ሱቆችን አዘምኖ የተሻለ ገቢ ለሚያስገኝ ተግባር ለማዋል እንዲቻል በትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡ በዚህም ከዚህ በፊት ለግለሰብ ተከራይተው የነበሩ የማህበሩን ቤቶች በማስለቀቅ፣ በማደስ እና በማዘመን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡ አሁን ላይ ማህበሩ አከራይቷቸው ከነበሩ 7 ቤቶች መካከል 6ቱን አስለቅቋል። ከእነዚህ ውስጥ ሦስት ቤቶች ዕድሳት እና ማሻሻያ ተደርጎላቸው ለተለያየ አገልግሎት (ለሱፐርማርኬት፣ የገላ መታጠቢያ ቤት..... ) ውለዋል፡፡ ቤቶቹ ከዚህ ቀደም ከ10 ሺህ እስከ 30 ሺህ ብር ይከራዩ ነበር፡፡ አሁን ላይ ወርሃዊ ገቢያቸው እስከ 100 ሺህ ብር ደርሷል። ይህንን ለውጥ መሰረት በማድረግ ቀሪ ቤቶችን የማዘመንንና ወደ አገልግሎት የማስገባቱ ተግባር ተጠናቅሮ ይቀጥላል። ቀሪው አንድ ቤትም ከሐምሌ 10 ቀን 2017 ዓ.ም. በኋላ የሚለቀቅ ይሆናል፡፡

የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ለከተማዋ ማህበረሰብ ትርጉም ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የገለጹት ደግሞ የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ ናቸው፡፡ ማህበራቱ የሚሰጡትን አገልግሎት የማዘመን፣ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የማራዘም እና ለተገልጋዩ ተደራሽነታቸውን የማሳደግ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ይህንንም ስኬታማ ለማድረግ ከኮሚሽኑ ጀምሮ እስከ መሰረታዊ ማህበራት ድረስ የአገልግሎት ስታንዳርድ የማሻሻልና የማስጠበቅ ሥራ ሳምንቱን ሙሉ ያለማቋረጥ በተቀናጀ መንገድ እየተከናወነ ስለመሆኑ አንስተዋል፡፡

የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት፣ የምርት አቅርቦትን በማሻሻል፣ ተደራሽነታቸውን በማስፋፋት እና የሕዝብ ሃብትን ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ እንዲውል ከማድረግ አንፃር የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት አይተኬ ሚና እየተጫወቱ ስለመሆናቸው የገለፁት ኮሚሽነሯ፤ በማህበራቱ የሚቀርቡ ምርቶች በነጋዴው ከሚቀርቡ ምርቶች አንፃር በዋጋ እና በጥራት የተሻሉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ ከሆነ፤ የመሰረታዊ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በቂ መጠን ያለው የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ ምርቶቹ በዋጋ ደረጃ በነጋዴው ከሚቀርቡት አንፃር ዝቅተኛ የሚባሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የጤፍ ዋጋ በኩንታል ከ2 ሺህ እስከ 2 ሺህ 500 ብር፣ ፓስታ እና መኮሮኒከ ከ10 እስከ 20 ብር፣ ጥራጥሬ በኪሎ ከ20 እስከ 30 ብር ቅናሽ አላቸው፡፡

ኮሚሽኑ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ከከተማ አስተዳደሩ በመረከብ ገቢያቸውን በሚያሻሽል (በሚያሳድግ) ተግባር ላይ እንዲያውሏቸው የተረከቧቸው ቢሆንም፤ አብዛኞቹን የገቢ ማስገኛ ተቋማት ለግለሰቦች በማከራየት፣ ገቢውን ለማህበሩ ከማስገባት ይልቅ ጥቂት አመራሮች ሲጠቀሙባቸው ቆይተዋል። ይህ አሠራር ደግሞ የሚጠበቀውን ውጤት እንዳላመጣ በተደረገ ክትትልና ግምገማ ተረጋግጧል። ከዚህ በመነሳት ማህበራቱ ያሏቸውን ገቢ ማስገኛዎች፤ በተለይም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቤቶች ከኪራይ በማስለቀቅ፣ በማዘመንና በማሻሻል ለተገቢው አገልግሎት እንዲውሉ የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠሉን ኮሚሽነሯ አስረድተዋል፡፡

የገቢ ማስገኛዎችን ከተከራዮች የማስለቀቅ፣ የማዘመን፣ የማሻሻል እና ለተሻለ አገልግሎት የማብቃት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ሰባት ወራትን ያስቆጠረ መሆኑን ያስታወሱት ኮሚሽነር ልዕልቲ፤ ይህ ተግባር ማህበራቱ በአሠራር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በአቅርቦት እና በተደራሽነት አቅማቸውን የማሳደግ፣ ለአባሎቻቸው እና ለከተማው ነዋሪ ተመራጭ አገልግሎት መስጠት የማስቻልን ዓላማ የያዘ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህብረት ስራ ማህበራት በራሳቸው ገፅ እና መልክ እንዲታወቁ ወጥ የሆነ የተቋማቱ መገለጫ (ሪብራንድ) ሥራም እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ የተሠራው ሥራ አበረታች ውጤት በማስገኘት ላይ ነው፡፡ የመንግስት እና የሕዝብ ሃብት ከግለሰቦች መጠቀሚያነት እንዲላቀቅ እና ለብዙሃኑ አገልግሎት እንዲውል እየተደረገ ነው። በዚህም ማህበራቱ አባሎቻቸው እና

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## የአረንጓዴ... ከገጽ 8 የዞረ

መቀነስ ማለት እንደሆነ አቶ መክብብ ያስረዳሉ፡፡

የችግኝ ተከላው ከመዝናኛ ፓርኮች ባሻገር ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን የሚሸፍን በመሆኑ ከዚህ ቀደም ውበት አልባ የነበሩ ወንዞች የህይወት ምንጭ እንዲሆኑ እያደረገ ነው፡፡ ከመነሻቸው ከእንጦጦ ጀምሮ በሚሰራው ስራ ወንዞች እየጠሩ፣ የድሮ ወዝና መልካቸውን እየያዙ መጥተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮና ሥነ ቀመር ኮሌጅ የአካባቢ ሳይንስ ማዕከል መምህርና ተመራማሪ የሆኑት መኩሪያ አርጋው (ፕሮፌሰር) ከአንድ ወር በፊት ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ 96 ነጥብ 3 ኤፍ ኤም፤ አጀንዳ ፕሮግራም ላይ በነበራቸው ቆይታ እንደገለፁት፣ የአረንጓዴ ዐሻራ በከተማዋ የከርሰ ምድር ውሃ አቅርቦት ዘላቂነት እንዲኖረው ትልቅ ፋይዳ ይጫወታል፡፡ ደኖች ሲመናመኑ በዛፎች አማካኝነት ወደ መሬት የሚሰርገው የውሃ መጠን ይቀንሳል፡፡ ይህም የከርሰ ምድር ውሃ መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል። ዛፎች ካልተተከሉ ለበርካታ ዓመታት እንዲያገለግሉ የሚቆፈሩ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች የውሃ አቅርቦት ይቀንሳል። ከዚህ አኳያ በከፍተኛ ቦታዎች የሚተከለው ዛፍ የሚወጣውን ውሃ መልሶ መተካት ያስችላል፡፡

የችግኝ ተከላው የቆሻሻ መጣያ በሆኑ፣ የተረሱ ስፍራዎች ላይ ጭምር የሚካሄድ በመሆኑ እነዚህ አካባቢዎች ንፁህ፣ አረንጓዴና ውብ ገፅታን ተላብሰው ሰዎች የሚዝናኑባቸውና መንፈሳቸውን የሚያድሱባቸው አካባቢዎች ሆነዋል፡፡ መኩሪያ (ፕ/ር) እንደሚሉት መንግስትና ህዝብን ከፍተኛ ወጪ ከሚጠይቁ ጉዳዮች አንዱ ጤናን ለመጠበቅ የሚወጣው የህክምና ወጪ ነው፡፡ የአረንጓዴ ሽፋን መጨመር፣ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎች ንፁህ መሆን ጤናን ለመጠበቅ በተለይ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም አረንጓዴ ስፍራዎች የሰለጠነ፣ ርዕይ ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ሰዎች ቁጭ ሲሉ ነው የሚፈጥሩት፡፡ ሰው ቆሻሻ ቦታ ላይ ተቀምጦ፣ ደስ የማይል ነገር እያየ ጥሩ ነገር ማሰብ አይችልም፡፡ ጥሩ የሚያስብና የተሻለ ለመስራት ዝንባሌ ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር እንደሚያግዝ የአካባቢ ሳይንስ ማዕከል መምህርና ተመራማሪው አብራርተዋል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ ማህበራዊ ጥቅሞችንም እያስገኘ እንደሆነ አቶ መክብብ ይገልፃሉ፡፡ በአንድ በኩል በችግኝ ተከላ ጊዜ በተለያየ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ አብረው የሚያሳልፉበትና የሚተዋወቁበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በተጨማሪም መዝናኛ ቦታዎች ውብ፣ አረንጓዴና ሳቢ በመሆናቸው የሰርግ፣ የልደትና የተለያዩ መርሀ ግብሮች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገናኙበት ሁኔታ በመፍጠር ማህበራዊ ትስስር እንዲጠናከር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

አረንጓዴ ዐሻራው በከተማ ደረጃ ውስን የነበሩ ችግኝ ጣቢያዎች፤ አሁን በየክፍለ ከተማው እንዲቋቋሙና በእነዚህ ጣቢያዎች ችግኝ እየፈላ፣ ችግኝ መትከል ባህል እየሆነ እንዲመጣ በር መክፈቱንም አቶ መክብብ ያነሳሉ፡፡

ባለፉት ዓመታት የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ ከተከናወነባቸው አካባቢዎች ጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል አንዱ ነው፡፡ ማዕከሉ 705 ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም አብዛኛው ስፍራ በባህር ዛፍ የተሸፈነ ነበር፡፡ በየዓመቱ ባህር ዛፉን በማንሳት በሀገር በቀል ዕፅዋት በመተካት በሚሰራው ስራ በአካባቢው ጠፍተው የነበሩ ምንጮች ተመልሰዋል። የዕፅዋት ዓይነቶችም ጨምረዋል፡፡ ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አዕዋፍትም ወደ ማዕከሉ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን አቶ መክብብ ያስረዳሉ፡፡

Addis Ababa Climate Action Plan (2021-2025) በሚል ርዕስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከC40 የከተሞች የአየር ንብረት አመራር ቡድን ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሰነድ እንደሚያሳየው በአዲስ አበባ የአረንጓዴ ቦታዎች ሽፋን መመናመን እስከ 40 በመቶ ለሚሆነው የጎርፍና የመሬት መንሸራተት አደጋዎች መከሰት አስተዋፅኦ አለው፡፡

ከዚህ አኳያ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የችግኝ ተከላና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች የጎርፍ አደጋ ስጋትን በመቀነስ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኝ አቶ መክብብ ያስረዳሉ። ለምሳሌ በጉለሌ ዕፅዋት ማዕከል በተራራማ ቦታዎች የሚፈጠረውን ጎርፍ ውሃ አቁረው የሚይዙ ጉድጓዶችን በመገንባት፣ የሚተርፈው ውሃ ደግሞ ተፈጥሯዊ ፍሰቱን ጠብቆ እንዲወርድ የጎርፍ መቀልበሻ በመስራት በታችኛው ተፋሰስ አካባቢ ያጋጥም የነበረውን ጎርፍ መከላከል ተችሏል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራው መርሀ ግብር ለበርካታ ወገኖችም የስራ ዕድል ፈጥሯል። አሁንም የጉለሌ ዕፅዋት ማዕከልን ለማሳያነት ብናነሳ ከዚህ ቀደም በአረንጓዴ ልማት የተሰማሩት ከ200 የማይበልጡ የቀን ሰራተኞች ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ700 በላይ ሰራተኞች በዕፅዋት ልማትና ብዜት፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ እንዲሁም በመዝናኛ ልማት ተሰማርተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ ሲጀመር የማዕከሉ የዕፅዋት ብዜት አቅም 100 ሺህ አልደረሰም ነበር። በ2012 ዓ.ም 550 ሺህ፣ 2013 ዓ.ም 560 ሺህ፣ በ2014 ዓ.ም 720 ሺህ እያለ እያደገ መጥቶ አሁን እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርስ ሀገር በቀል የዕፅዋት ችግኝ በማባዛት ማቅረብ ተችሏል፡፡ ችግኝ የሚፈላበት ስፍራ በዓመት ዜሮ ነጥብ ስምንት ሄክታር ከነበረበት ወደ ሶስት ሄክታር ማሳደግ እንደተቻለ አቶ መክብብ አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ለችግኝ ተከላ የሚካሄደው ቅድመ ዝግጅትም ተሻሽሏል፡፡ ችግኝ መትከል ባህል እየሆነ መጥቷል፡፡ ከተከላ በኋላ ያለው እንክብካቤ ላይ መሻሻሎች ቢኖርም አሁንም ክፍተቶች አሉ፡፡ ከዚህ አኳያ “ከተከልን መንከባከብ አለብን” በሚል መርህ መስራት እንደሚገባ አቶ መክብብ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የችግኝ ተከላና የአረንጓዴ ሽፋን መጨመር ለአዲስ አበባ ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው ተግባር ነው፡፡ የከተማዋን እስትንፋስ የማስቀጠል፣ ውበቷንና የዜጎችን ጤና የማስጠበቅ፣ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ቱሪዝምን የማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጉዳይ ነው፡፡ በጥቅሉ ከተማዋን ለኑሮ ምቹና ተስማሚ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት የሚያግዝ ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡

## እፎይታን... ከገጽ 11 የዞረ

ታካሚዎችን ለማስተናገድ የመሰረተ ልማት (በቂ የአስተኝቶ ህክምና አልጋዎችና ሌሎች ግብአቶች) አለመሟላት ፈተና ሆኖ ቆይቷል። በሆስፒታሉ ያለውን አጠቃላይ አገልግሎት ለማስፋትም ከምድር በታች ያለውን ሳይጨምር ባለ 8 ወለል የማስፋፊያ ህንፃ ግንባታ ተጠናቅቋል፤ በ2018 በጀት ዓመት ይመረቃል፡፡ ይህም በሆስፒታሉ የሚሰጠውን የኩላሊት እጥበት ህክምና በስፋት ለመስጠት ዕድል እንደሚፈጥር ዶክተር ዮሐንስ ጠቁመዋል፡፡

ለአዳጊ ሀገራት ብቻ ሳይሆን በእድገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለደረሱት የኩላሊት እጥበት ውድ ህክምና ነው፡፡ አዋጪው የኩላሊት ንቅለ ተከላ ማከናወን ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፣ አገልግሎቱ በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል ይሰጣል፡፡ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታልም ንቅለ ተከላውን ለማከናወን አስቀድሞ የተደራጀ የኩላሊት እጥበት አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላ የንቅለ ተከላ ህክምናው ይጀመራል፡፡ አንድ ሰው ቦታውን ለሌላ ታካሚ የሚለቀው የንቅለ ተከላ ህክምናውን ሲያገኝ ነው። እንደሀገርም የንቅለ ተከላ ህክምናውን አጠናክሮ መቀጠል አዋጪ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የኩላሊት ህሙማንን ጫና ለማቃለል ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እንዳደረገው ሌሎችም ድርጅቶች ወይም ባለድርሻ አካላት በዚህ ዓይነት የበጎነት ስራ በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ዶክተር ዮሐንስ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ከዚህ በፊት የኩላሊት ህመም ተጋላጭ የሚሆኑት በእድሜ የገፉ ሰዎች ነበሩ፡፡ አሁን ግን በህፃናትም ዘንድ ህመሙ እያጋጠመ ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በየጊዜው የጤና ምርመራ በማድረግ በኋላ ሊያጋጥም ከሚችል ስር የሰደደ የኩላሊት ህመም ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።

ከዚህ ባለፈ ከልክ በላይ ክብደትን መቀነስ፣ ቅባታማና ጨው የበዛባቸው ምግቦችን ባለመመገብ እንዲሁም አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ህመሙን መከላከል እንደሚቻል ሲስተር ህይወት ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

## ማህበራቱ... ከገጽ 16 የዞረ

ሌሎች የከተማዋ ነዋሪዎች የተሻለ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው፡፡

ኮሚሽነሯ አክለው እንዳብራሩት፤ የተዘዋዋሪ ብድር አቅርቦትን በመጠቀም የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ወቅቱን የጠበቀ ግዢ በመፈፀም በብዛት የማስገባት ተግባር ተጠናክሮ ቀጥሏል። በከተማ አስተዳደሩ ያሉ 11 ዩኒየኖች እና 154 መሰረታዊ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በቂ ምርት ክምችት ዓመቱን ሙሉ በመያዝ ለሸማቹ እያቀረቡ ይገኛሉ። በያዝነው የክረምት ወቅትም ያለ አንዳች የአቅርቦት እጥረት ምርቶችን ለሸማቹ ማቅረብ የሚችሉበት አቅም ላይ ይገኛሉ፡፡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች በሁሉም የማህበራት ሱቆች፣ ከ140 አካባቢ በደረሱ የቅዳሜና እሁድ የግብይት መዳረሻ ቦታዎች እንዲሁም በዓላትን መሰረት በማድረግ በሚዘጋጁ ባዛሮች ላይ ማህበራቱ ለሸማቹ ማቅረባቸውን ቀጥለውበታል፡፡

የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲሻሻል ለማድረግ ኮሚሽኑ የጀመረውን የሪፎርም ትግበራ ሂደት አጠናክሮ እንደሚቀጥል የጠቆሙት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር፤ ለተጀመረው ሥራ ስኬታማነት በቅርቡ እንደከተማ ተዘጋጅቶ የወረደው የ90 (ዘጠና) ቀናት ዕቅድ ትልቅ አቅም እንደሚሆንላቸው ገልፀዋል፡፡ ይህም ከመደበኛው ዕቅድ በተጓዳኝ በምርት ግዢ እና ስርጭት ዕቅድ ከፍተኛ መጠን ያለው ግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ግዢና ስርጭት እንዲከናወን፣ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራትን አገልግሎት እንዲሻሻል፣ የገቢ ማስገኛ ተቋማቱ እንዲዘምኑና ወቅቱን የሚመጥን ግልጋሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ተግባራት እንዲከናወኑ አቅም እንደሚፈጥር አስረድተዋል፡፡

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉ መሰረታዊ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በአጠቃላይ ከ2 ሺህ 800 በላይ የገቢ ማስገኛ ተቋማት አላቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በግለሰቦች ኪራይ የተያዙት ከ1 ሺህ 500 በላይ ሲሆኑ፤ በሰባት ወራት ውስጥ 570 የሚሆኑትን ማስለቀቅ ተችሏል፡፡ ከተለቀቁት ውስጥ 90ዎቹ ገቢ ማስገኛ ተቋማት በማደስና በማዘመን ለተሻለ አገልግሎት ብቁ ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ ተቋማትም ህብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች (የዳቦ ቤት፣ የወፍጮ፣ የሱፐርማርኬት፣ የፍሬሽ ኮርነር፣ የሻውር...) በጥራት እና በስፋት ማዳረስ ተችሏል፡፡ ይህ ተግባር በዘጠና ቀናት ዕቅድ ውስጥ ተካትቶ ፍጥነትንና ጥራትን ያማከለ ከፍተኛ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ከላይ እስከ ታች ባሉ የኮሚሽኑ አመራሮች እና ባለሙያዎች ሌሊት እና ቀን እየተሠራ ነው፡፡

የተለያዩ ግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ከአምራች አርሶ አደር ዩኒየኖች እና ከኢንዱስትሪዎች የማስገባቱ እና ለተጠቃሚዎች የማዳረስ ተግባር በመከናወን ላይ ነው፡፡ ማህበራቱ ምርቶችን የሚገዙበትን ገንዘብ ቀድሞ የወሰዱትን የተዘዋዋሪ ብድር እየመለሱ በአዲስ በመውሰድ ግዢ የሚፈፅሙበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ በዚህም እንደ አራዳ፣ ቂርቆስ፣ ኮልፌ፣ ቦሌ፣ ልደታ ክፍለ ከተሞች ያሉ የሸማች ህብረት ሥራ ዩኒየኖች ገንዘቡን በመውሰድ ወደ ግዢ ሂደት ገብተዋል፡፡ ሌሎቹም በዚሁ ፍጥነት ወደተመሳሳይ ሂደት ውስጥ ይገባሉ፡፡

እንደከተማ አስተዳደር ቁጥራቸው ከግማሽ ሚሊዮን የሚበልጡ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት አባላት ያሉት ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ከ25 ሺህ በላይ የሚሆኑት በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ (ፋይዳ) እንዲወስዱ እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ኮሚሽነሯ፤ የሸማቹን ማህበረሰብ ፍላጎት ለማሟላት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ እና ቀጣይነት እንዲኖረው በየደረጃው ያለ አመራር፣ ዩኒየኖች፣ መሰረታዊ ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እና አባላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ለህብረት ስራ ማህበራት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የአዲስ አበባ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የስራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን በቅርቡ ባካሄደበት ወቅት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች የአስተዳደራቸውን የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ሲያቀርቡ የተናገሩትም ይኸንኑ የሚያጠናክር ነው። እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፣ የአዲስ አበባ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ይስተዋል የነበረውን የሌብነትና ብልሹ አሰራር፣ የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት አሰጣጥ እና ተጠያቂነትን ያለማስፈን ችግሮችን በሚፈታ አግባብ የኢንስፔክሽን እና የኦዲት ሥራዎች እንዲሰሩ ተደርጓል። በኦዲት የተገኙ ጉድለቶችን በፍርድ ቤት፣ በሽምግልና ዳኝነት እና በምክክር ከ17 ሚሊዮን ብር በላይ ተመላሽ ማድረግ ተችሏል። የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ምርቶች እንዲያቀርቡ በማድረግ የግብይት መጠናቸውን ብር 13 ቢሊዮን 355 ሚሊዮን 642 ሺህ 359 ለማድረስ ታቅዶ ብር 14 ቢሊዮን 090 ሚሊዮን 109 ሺህ 025 ማከናወን ተችሏል፡፡

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ እንደገና አንተነህ ተስፋው ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) AA000080600135840325 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 225100 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የካርታ ቁጥር የካ/219572/11/227/13 በሴሪ ቁጥር 0252194 በእነ በድልዋ መሀሪ ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ እገዳ ይዤዋለሁ የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ት ሰላም ባህረ ሀዲሽ እና ወርቁ ሀይሉ እንግዳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የካርታ ቁጥር ቦሌ 14/296/6/31499/00 የሴሪ ቁጥር 034473 ተመዝግቦ የነበረው ኦርጅናል የይዞታ ማህደር ፍርድቤት ጠይቆ ተልኮ ነበር ነገር ግን የግል ማህደራቸው እንዲመለስ ስንጠይቅ ጠፍቶአል ተብሎ ሊመለስ አልቻለም በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለይዞታ ማህደር አስተዳደር ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ማህደር የሚከፈትላቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ገነት ወርቄ ወልደስላሴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007337425O216 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኢብራሂም መሐመድ ኢብራሂም ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር ሀ3-113 የመሬት ይዞታ ካርታ ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000040301387 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን /ዘጠና ቀን/ ድረስ ጽ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካልቀረቡ ግን በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ታደለ አንተነህ በየነ ስም በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር ቦሌ6/26/4/7/31-1623/38-2297/3556/03 በሴሪ ቁጥር 016545 የተሰጠበት ቀን 07/08/03 የሆነ ማህደር በማህደር ክፍላችን ውስጥ ማግኘት ባለመቻሉ ማህደራቸውን ይዥዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ቀርበው እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ፀሀይ ከፍአለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የካርታ ቁጥር ቦሌ10/67/3909/00 ሴሪ ቁጥር 000714 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 09 ቀበሌ 12 በአዲሱ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 901 በአቶ ወርቅአገኘሁ ምስጋናው ስም የወጣው ቁጥሩ አ/08/34/8135/01 በቀን 12/10/06 ዓ.ም ወጪ የሆነ ዋና ካርታ ስለጠፋባቸው በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 08/11/2017 ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ/11/121/6/1/322527/00 ሴሪ ቁጥር 1571786 በአቶ ብርሀኑ አሸናፊ ፈንታቢል ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ክበብ ገብረእግዚአብሔር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 022230/1 የሴሪ ቁጥር 029815 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ15/06 በቀን 11/03/17 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ግዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቱሉ ዲምቱ 2 ውስጥ በካርታ ቁጥር 041307 በሴሪ ቁጥር 117762 በ ወ/ሮ ጽጌ ሲራክ ገ/መስቀል የተመዘገበ ይዞታ ከማህደር ክፍላችን የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች እየሩሳሌም መሃሪ በቀን 27/10/2017 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ቦሌ10 /2/1//4/1/4006/54353/180045/213384/03 በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የሴሪ ቁጥር 0161115 ወረዳ 10 የቦታው ስፋት 249 ሜ.ካ የሆነው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡

አመልካች እየሩሳሌም መሃሪ በቀን 27/10/2017 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ቦሌ10 /2/1//4/1/4006/54353/180045/213384/03 በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የሴሪ ቁጥር 0161115 ወረዳ 10 የቦታው ስፋት 249 ሜ.ካ የሆነው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው ካርታ የጠፋ መሆኑን ያመለከቱ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ የትምወርቅ አየለ በየነ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090604054 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ 08/11/2017 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያሳወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በወረዳ 11 በ መንግስቱ ማሞ ጉደታ እና ገነት ከፈኒ ከሌቻ ስም የተመዘገበ የይዞታው መለያ ቁጥሩ AA00005 1102182 የተሰጠበት ቀን 20/07/2011 ዓ.ም እና ሴሪ ቁጥር L 031393 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካ/ፖ/ወ/ቁራ/130 በቀን 07/11/2017 ዓ.ም የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አድማስ ቦርሲዶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 02413 የሴሪ ቁጥር 025231 የይዞታ ስፋት 175 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር መመ15/18656/17 በቀን 21/06/2017 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የከተማ... ከገጽ 9 የዞረ

ይደረግላቸዋል፡፡

በኮሚሽኑ የዕፅዋት ቴክኖሎጂ ግብአት አቅርቦት አመቻች ባለሙያ አቶ ኢሳያስ አበበ በተመሳሳይ እንደገለፁት፤ በከተማ ግብርና ዘርፍ በአብዛኛው በጓሮ አትክልት፣ በሰብልና ሌሎችም ላይ እየሰሩ ለሚገኙ አካላት የተሻለ ውጤት እንዲያገኙ፣ ምርትን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ አሰራሮችን እንዲከተሉ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ይህም ሥነ ምህዳርን መሰረት በማድረግ የትኛው አካባቢ የተሻለ ምርት እንደሚሰጥ፣ በመስመር መዝራት፣ ዘር ሲዘራና ከተዘራ በኋላ በምን መልኩ ክትትል መደረግ እንዳለበት እና ሌሎችም ላይ የማማከር ስራ ይሰራል፡፡ አርሶ አደሮች በተመጣጣኝ ዋጋ ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የማመቻቸት ስራም በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ ባለፈ በከተማ ግብርና የተሰማሩ አርሶ አደሮች ማሳ ላይ መስሪያ ቦታቸው ድረስ በመውረድ የማዳበሪያ አጣጣል፣ የዘር አጠቃቀም፣ የተባይና የበሽታ ቁጥጥር ላይ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን ባለሙያው ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር እና የኤክስቴንሽን ዘርፍ ኃላፊ አቶ መለሰ አንሼቦ እንደገለፁት፤ ከሀገራዊ ለውጡ በፊት የከተማ ግብርና ዘርፍ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ስር በዳይሬክቶሬት ደረጃ ሆኖ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ከለውጡ ወዲህ መንግስት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ በ2011 ዓ.ም "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን" በሚል ስያሜ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም አድርጓል። በዚህም በከተማ ግብርና በዋናነት በእንስሳት ዘርፍ የእንቁላል፣ የዶሮ ስጋ፣ የበሬ፣ የበግና ፍየል ስጋ፣ የማርና የዓሳ ምርቶች ትኩረት ተደርጎ እየተሰራባቸው ነው፡፡ በዕፅዋት ዘርፍ ደግሞ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ የሚመረቱ የአትክልት እና ፍራፍሬ እንዲሁም የሰብል ምርቶች፣ ከአርሶ አደሩ ማሳ ውጪ ደግሞ በከተማ ውስጥ በሚከናወኑ የአትክልት ምርቶችና በሌሎችም ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዘርፉ ውጤት ለማምጣት የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን አቶ መለሰ ያስረዳሉ፡፡ ለአብነት የግብርና መዋቅሩን ከከተማ እስከ ወረዳ በየደረጃው መዘርጋት፣ በእንስሳት እርባታ፣ በዕፅዋት ልማት፣ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ በባለሙያዎችም የግብርና ስራ በከተማ ውስጥ እንዴት ማከናወን እንደሚቻልና ፍላጎቱ ያላቸው ወደ ዘርፉ ገብተው እንዲሰሩ የማስተማር፣ የስልጠናና የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ይጠቀሳሉ፡፡

በተጨማሪም በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት ግብአት እንዲያገኙ የማመቻቸት ስራ የሚሰራ ሲሆን ለአብነት በዶሮ እርባታ ለሚሰማሩ የእንቁላል ጣይ ዶሮ እና የዶሮ ጫጩት ከሚያቀርቡ አካላት ጋር በማስተሳሰር ግብአቶቹን ካገኙ በኋላ በምን መልክ ማምረት እንዳለባቸው ስልጠና ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የእንስሳት መኖ፣ ማዳበሪያ እንዲቀርብ የማድረግና ሌሎችም የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ ተግባራት በመከናወናቸው በአሁኑ ወቅት በእንስሳት እና በዕፅዋት ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች 1 ሚሊዮን 28 ሺህ ደርሰዋል፡፡ ይህ ትልቅ ውጤት ነው ብለዋል፡፡

ምክትል ኮሚሽነሩ እንዳስረዱት፤ ከተማ ለመኖሪያነት፣ ለንግድና ለሌሎች ክዋኔዎች የሚሆን እንጂ ለግብርና ስራ ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም። መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረት ይህ አመለካከት ተቀይሮ፤ የከተማ ግብርና ተተግብሮ ውጤት ከማምጣቱ ባሻገር ባህል ሆኖ እየተሰራበት ያለ ዘርፍ ሆኗል። በመሆኑም በአዲስ አበባ ከተማ አሁን ላይ እንቁላል ለቤተሰብ ፍጆታ በግላቸው የሚያመርቱ እና ተደራጅተው ለገበያ የሚያቀርቡ ያሉ ሲሆን በከተማዋ በቀን ከ2 ሚሊዮን በላይ እንቁላል ይመረታል።ከዚህ ውስጥ ከፍጆታ አልፎ ከ509 ሺህ በላይ እንቁላል ለገበያ ይቀርባል፡፡ ወተት በቀን ከ100 ሺህ ሊትር በላይ ይመረታል፡፡ ሌሎችም ምርቶች ለገበያ እየቀረቡ በመሆኑ የከተማ ግብርና ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ በከተማ ግብርና ዘርፉም በ2013 ዓ.ም 109 ሺህ 347፣ በ2014 ዓ.ም 289 ሺህ 763፣ በ2015 ዓ.ም 423 ሺህ 95፤ በ2016 ዓ.ም 721 ሺህ 905 እንዲሁም በ2017 ዓ.ም 1 ሚሊየን 28 ሺህ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በእንስሳት ዘርፍ የተሰማሩ አካላት እየተደረገላቸው ያለው ድጋፍ የሚበረታታ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን የእንስሳት መኖ ዋጋ መናር ስራቸውን በሚፈለገው ልክ ለማከናወን ተግዳሮት መፍጠሩን አንስተዋል፡፡ ለዚህ ምን ምላሽ አለዎት? ላልናቸው ጥያቄ ምክትል ኮሚሽነሩ በሰጡት ምላሽ፣ "ትክክል ነው፤ የመኖ ዋጋ መናር መኖሩ ይታወቃል። የዋጋ መናሩ እየተከሰተ ያለው በሁለት ምክንያቶች ነው፤ ለመኖ ማቀነባበሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ዋጋ መጨመር እና ከዚህ በፊት ያልነበረ 15 በመቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) በመኖ ላይ በመጨመሩ ነው፡፡ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ሙሌ የመኖ ማቀነባበሪያ የተሰኘ መኖ ባህር ዳር አምርቶ አዲስ አበባ አምጥቶ የሚሸጥ ካምፓኒ በቦሌ ክፍለ ከተማ በመንግስት ቦታ ተሰጥቶት 50 ሺህ ኩንታል መያዝ የሚችል መጋዘን በመገንባት እያመረተ እንዲያቀርብ ውል ተደረገ፡፡ በዚህም መሰረት የደላሎች እጅ ሳይገባበት መኖው በመዲናዋ የሚገኙ አምራቾችና አከፋፋዮች ከሚሸጡበት በዝቅተኛው ዋጋ ምርቱን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ 25 ሸማች ሱቆች በኩል ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብ እየተደረገ ነው። ከፍ ያለ ቁጥር የሚጠቀሙት ደግሞ ከመጋዘኑ እየመጡ እንዲገዙ ይደረጋል፡፡ ይህ ማለት ግን የመኖ ዋጋ ንረትን ፈትተናል ማለት አይደለም፡፡

ከዚህ ባለፈ የውሃ እጥረት እንዳለ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት ከዚህ ቀደም ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ የውሃ ቦቴዎች በከተማ አስተዳደሩ ስላሉ ቦቴዎቹን ተረክበን በእንስሳትና በእፅዋት ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ውሃ ለማቅረብ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የከርሰ ምድር ውሃ በማውጣት እንዲጠቀሙ ለማድረግ የማመቻቸት ስራም እየተከናወነ ይገኛል" ብለዋል፡፡

በከተማ ግብርና ዘርፍ በመሰማራት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል በባለሙያ ግንዛቤ የተሰጠ ቢሆንም ስራ ከጀመርን በኋላ ያመጣነውን ውጤት በሚፈለገው ሁኔታ ወርደው ማየት ቢችሉ እንበረታታለን በሚል ለተነሳው አስተያየት አቶ መለሰ ሲመልሱ፤ "በወረዳ፤ በክፍለ ከተማና በከተማ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎች ወርደው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ። ነገር ግን በከተማ ግብርና ዘርፍ የተሰማሩ አካላት ከአንድ ሚሊዮን በላይ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው ጋር ለመድረስ የባለሙያ እጥረት አለ። በወረዳም እጥረቱ ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪም ባለሙያዎች በዘርፉ ስራ ላይ ያለመቆየት ችግርም አለ፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር ለመቅረፍ መዋቅሩን በማየት ጥናት ተደርጎ ባለሙያዎች እንዲሟሉ በትኩረት ይሰራል" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የከተማ ግብርና ዘርፍን ለማስፋፋት በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የሚደረጉ ማንኛውም የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ማስቀጠል፣ ችግሮቻቸውን በመለየት መፍትሔ የመስጠትና ሌሎችም ስራዎች በትኩረት የሚሰሩ መሆናቸውን የሚገልፁት አቶ መለሰ፣ በግቢው ሰፊም ይሁን ጠባብ ቦታ ያለው ማንኛውም ህብረተሰብ የከተማ ግብርናን ማከናወን ስለሚቻል ጠንክሮ በመስራት ከጓሮው ትኩስና ንፁህ ምርት በማምረት ለእለት ጉርሱ ተጠቃሚ እንዲሆን መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በ2022 ዓ.ም አዲስ አበባ የከተማ ግብርና የተስፋፋባት፤ የአርሶ አደሩ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት እና ከአፍሪካ ከተሞች በዘርፉ ተምሳሌት የሆነች ከተማ የማድረግ ርዕይ ተይዞ እየተሰራ መሆኑንም ምክትል ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል፡፡

# ማስታወቂያ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 12 በቀድሞ ወረዳ 25 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 9999/1 ለሆነው ቤት የካርታ ቁጥር ወ13/ውዝ01/571/14142/00 በሴሪ ቁጥር 013825 ሰፈረ ገነት ገና መረዳጃ እድር ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት የሙብት ፈጠራና የይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 አንቀጽ 23 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ30 (ሰላሳ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 (በሰላሳ ቀን) ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትክ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች ዳዊት ጥጋቡና ሰብለ ወርቁ በተዋከይያቸው ሰለሞን አመንሽዋ በቀን 27/09/2017 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ቦሌ16/104/1835/00 በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የሴሪ ቁጥር 016307 የቦታው ስፋት 300 ሜ.ካ የሆነው ካርታ የተሰጣቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡

አመልካች ዳዊት ጥጋቡና ሰብለ ወርቁ በተዋከይያቸው ሰለሞን አመንሽዋ በቀን 27/09/2017 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ቦሌ16/104/1835/00 በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የሴሪ ቁጥር 016307 የቦታው ስፋት 300 ሜ.ካ የሆነው ካርታ የሆነው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው ካርታ የጠፋ መሆኑን ያመለከቱ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ በአቶ ሬድዋን መሐመድ ራህመቶ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) AA000021001294 በቀን 29/12/2009 ሴሪ ቁጥር 007727 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 09/11/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይገኙዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ 90 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

# የነገዎቹ ከዋክብት በናይጄሪያ

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ በሴቶች ከ18 ዓመት በታች 3 ሺህ ሜትር የብርና የነሀስ ሜዳልያ ባገኘችበት ወቅት

እንደ ኢትዮጵያ፣ ኬኒያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሞሮኮ ያሉ የአፍሪካ ሀገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝና ካተረፉባቸው የስፖርት ዘርፎች መካከል የአትሌቲክስ ስፖርት አንዱ ነው፡፡ ምሩጽ ይፍጠር፣ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባ የኢትዮጵያን ስም በመልካም ካስጠሩ አንጋፋ አትሌቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነዚህ የአፍሪካ ሀገራት ውጤታማ ለመሆናቸው ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ደግሞ በየጊዜው አዳጊዎችን እየተኩ በመሆናቸውና በየዕድሜ እርከኑም ውድድሮች በማካሄዳቸው ስለመሆኑ ይገለጻል፡፡ ለዚህም የአፍሪካ አዳጊዎች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በመባል የሚታወቀውና በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች ሻምፒዮና ተጠቃሽ ነው፡፡

የአፍሪካ ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ሻምፒዮና የአትሌቲክሱ ጌጥ የሆኑ ተተኪ አፍሪካውያን አትሌቶች የሚለዩበት ታላቅ መድረክ ነው፡፡ የአሁኖቹን ኢትዮጵያውያን ከዋክብት ዮሚፍ ቀጀልቻ፣ ሰለሞን ባረጋ፣ ቢኒያም መኸሪ ያሉ አትሌቶችን መጀመሪያ ዓለም የተመለከታቸው በዚሁ ውድድር ላይ መሆኑን በአስረጅነት መጥቀስ ይቻላል። እንደዚሁም እንደ ድርቤ ወልተጂ፣ ዘርፌ ወንድማገኝ፣ አይናዲስ መብራቱ እና ለሜቻ ግርማን የመሳሰሉ አትሌቶች የተገኙበት ውድደር ነው፡፡

ሐምሌ 9 ቀን 2017 ዓ.ም የተጀመረውና እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2017 ዓ.ም የሚቆየው የዘንድሮው ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የአህጉሪቱ የአትሌቲክስ ባለተሰጥኦዎች የሚለዩበት ነው ተብሎ ይጠበቃል።

የአፍሪካ 20 ዓመት በታች ውድድር በአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን አዘጋጅነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው እ.ኤ.አ በ1994 ነበር፡፡ ከ20 ዓመት በታች 13 መድረኮችን ከ18 ዓመት በታች ደግሞ ሁለት ውድድሮችን ከዚህ ቀደም አከናውነዋል፡፡

በእስካሁኑ ውድድርም ደቡብ አፍሪካ 229 ሜዳልያዎችን በማግኘት ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃን ስትይዝ ኬኒያ 189 ሜዳልያዎች፣ ናይጄሪያ በ181 ሜዳልያዎች በመያዝ በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያም በ175 ሜዳልያዎች በአራተኛ ደረጃ ተቀምጣለች፡፡

በናይጄሪያዋ ከተማ እየተካሄደ ባለው የአፍሪካ ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ከ43 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ 937 አትሌቶች በሁለቱም ፆታዎች እየተወዳደሩ ይገኛሉ፡፡ አዘጋጇ ሀገር ናይጄሪያ 60 ወንዶችና 50 ሴቶች በድምሩ 110 አትሌቶችን በማሳተፍ ቀዳሚዋ ሆናለች። ኢትዮጵያ ደግሞ 8 ወንዶችና 20 ሴቶች በድምሩ 28 አትሌቶችን በመያዝ እየተሳተፈች ትገኛለች።

የአፍሪካ ታላላቅ የአትሌቲክስ ስፖርተኞች መፍለቂያ የሆኑት እንደ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬኒያ፣ ኢትዮጵያ እና ግብጽ ያሉ ሀገራት ደግሞ ቀዳሚ ግምት ያገኙ ሀገራት ናቸው። ከእነዚህ ሀገራት በተጨማሪም ጋና፣ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ካሜሩን፣ ሴኔጋል እና ኡጋንዳ ጠንካራ ፉክክር እያደረጉ ይገኛሉ።

የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ኦፍ ናይጄሪያ (AFN) ፕሬዝዳንት እና የኮንፌዴሬሽን ኦፍ አፍሪካ አትሌቲክስ (CAA) ምክትል ፕሬዝዳንት የሆኑት ቶናቦክ ኦኮዋ ዝግጅቱ በሚፈለገው ልክ መሆኑን መታዘባቸውን ገልጸዋል። በአፍሪካ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (CAA) ዕውቅና የተሰጠው ይህ ሻምፒዮና የአፍሪካን ቀጣይ ትውልድ የአትሌቲክስ ሻምፒዮና በማጉላት የተሻሉ አትሌቶች የሚታዩበት እንደሚሆን ነው የተገለጸው።

በዚህ መድረክ ላይ ኢትዮጵያን የሚወክለው ልዑክ በሁለት ተከፍሎ ወደ ናይጄሪያ ያመራ ሲሆን፣ ኢትጵያውያን አትሌቶች በ16 ዘርፎች ይካፈላሉ፡፡ ከ18 ዓመት በታች በስምንት በተመሳሳይ ከ20 ዓመት በታች በስምንት የማጣሪያ እና የፍጻሜ ፍልሚያዎችን ያደርጋሉ፡፡

ይህን መረጃ እስካጠናቀርንበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ በተሳተፈችባቸው ውድድሮች ሜዳልያዎችን አግኝታለች፡፡ በ3 ሺህ ሜትር ሴቶች ከ18 ዓመት በታች ውድድር ደስታ ታደለ 2ኛ እንዲሁም ብርነሽ ደሴ 3ኛ በመውጣት የብር እና ነሃስ ሜዳልያ አስገኝተዋል፡፡

በ1 ሺህ 500 ሜትር ከ18 ዓመት በታች ሴቶች ኤልሳቤጥ አማረ የብር ሜዳልያ ስታገኝ፣ ደስታ ታደሰ የነሃስ ሜዳልያ ማግኘት ችላለች። በ1 ሺህ 500 ሜትር ወንድ ከ18 ዓመት በታች ሳሙኤል ገብረሃዋርያ የነሃስ ሜዳልያ አምጥቷል። በ3 ሺህ ሜትር ሴቶች ከ20 ዓመት በታች ፍፃሜ ውድድር ደግሞ ትርሃስ ገ/ሕይወት 2ኛ በመውጣት የብር ሜዳልያ ስታገኝ ውድነሽ ዓለሙ 4ኛ፣ ቤተልሔም ጥላሁን 6ኛ ደረጃ ይዘው አጠናቀዋል፡፡ እንደዚሁም የሴቶች ከ18 ዓመት በታች 3 ሺህ ሜትር ፍጻሜ አትሌት ደስታ ታደለ 2ኛ በመውጣት የብር ሜዳልያ ስታገኝ፤ ብርነሽ ደሴ የነሃስ ሜዳልያ ማግኘቷን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሳውቋል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በዚህ ውድድር ላይ በርካታ ድሎችን ያሳካች ሲሆን በተለይ እ.ኤ.አ በ2023 የዛምቢያ ንዶላ መድረክ የአረንጓዴው ጎርፍ ከታየባቸው ሦስት ርቀቶች መካከል ከ20 ዓመት በታች የሴቶች 3 ሺህ ሜትር አንደኛው ነበር፡፡ በአቢጃኑ የመጀመሪያ ውድድር ኢትዮጵያ በ6 ወርቅ፣ በ10 ብር እና በ14 ነሃስ በድምሩ በ30 ሜዳልያ አምስተኛ ሆና ነው ያጠናቀቀችው። ከሁለት ዓመታት በፊት በተደረገው የንዶላው መድረክ ደግሞ 4 ወርቅ፣ 7 ብር እና 4 ነሃስ ጠቅላላ 15 ሜዳልያዎችን በመሰብሰብ አራተኛ ደረጃን በመያዝ ስለማጠናቀቋ የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን መረጃ ያሳያል።

በእርግጥ በዚህ ውድድር ከዕድሜ ተገቢነት ጋር በተያያዘ ችግር የነበረባቸው አትሌቶች በመቀነሳቸው ምክንያት የአትሌቶች ቁጥር ከወትሮው ያነሰ በመሆኑ በውጤቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ተገልጿል፡፡ በተገቢው የዕድሜ እርከን በቴክኖሎጂ የታገዘ ስልጠና አለመኖሩ አሁን ለተፈጠረው ችግር ምክንያት ቢሆንም በውድድሩ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሰሩ የልዑካን ቡድኑ አሰልጣኞች አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንደሚገልፀው ለዓመታት በአትሌቲክስ ዘርፍ የነበረውን የእድሜ ተገቢነት ችግር ለመቅረፍ፤ በርካታ ሥራዎች እየሠራ እንደሚገኝ እና በናይጄሪያ በሚደረገው መድረክም የሚሳተፉ አትሌቶች በትክክለኛው መንገድ የተመረጡ መሆናቸውን ነው።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና አቃቤ ነዋይ ወይዘሮ አበባ ዮሴፍ ፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያ ፖሊስ ሆስፒታል ለ88 አትሌቶች የዕድሜ ምርመራ ያደረገ ሲሆን፣ 28 አትሌቶች ከ20 ዓመት በላይ መሆናቸው መረጋገጡን አንስተው፣ ፌዴሬሽኑ አሁንም ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት በዕድሜ ተገቢነት ጉዳይ ላይ አበክሮ እንደሚሰራ ጠቅሰዋል።

በናይጄሪያዋ አቡኩታ ከተማ የተካሄደው 31ኛው መደበኛ ኮንግረስ በዓለም አትሌቲክስ ፕሬዝዳንት ሎርድ ሰባስቲያን ኮ የቪድዮ መልዕክት የተከፈተ ሲሆን፣ በጉባኤው የ2024 የኮንፌዴሬሽኑ የክንውን ሪፖርት ቀርቧል። ከጉባኤው ተሳታፊዎችም “ኢትዮጵያ በእድሜ ተገቢነት” ላይ እየወሰደች ያለችው ስራና ቁርጠኝነት እንዲሁም እርምጃ አድናቆት የተሰጠው ሲሆን፣ ለሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እንደሚሆን ተገልጿል።

ሻምፒዮናው ከናይጄሪያ ዋና ከተማ ሌጎስ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘውና 10 ሺህ ተመልካቾችን በሚያ ስተናግደው ኤም.ኬ.ኦ ኢንተርናሽናል ስቴድየም ነው እየተከናወነ የሚገኘው፡፡

